# ትንሣኤ

③ ስሙነ ሕማማት
ጸሎተ ሐሙስ...ቀዳም ሥዑር

④ የግንቦት ልደታ ንፍር
በግንቦት ሠርግ አለመኖር

① የቅዱስ ዮሐንስ በዐል
አከባበር (እንቁጣጣሽ)

② ጾመ ገሃድ
ጾመ ሕርቃል

⑤ ቡሄ

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፱

www.ethiopianorthodox.org


# ትንሣኤ

፪ኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፫

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ በ፴፪ኛው ዘመነ መንግሥታቸው

በብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

ታኅሣሥ ፲፱፻፶፬ ዓ ም ታተመ ።



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ፤

አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

አርእስት ። ገጽ


፩/ ቅዱስ ዮሐንስ ፤ ............ ፯—፲፱

፪/ ጾመ ገሃድና ጾመ ሕርቃል ፤ ............ ፳—፳፭

፫/ ስሙነ ሕማማት ፤ ............ ፳፮—፳፰

፬/ ጸሎተ ሐሙስ ፤ ............ ፳፱—፴፪

፭/ ቀዳም ሥዑር ፤ ............ ፴፫—፴፭

፮/ የግንቦት ልደታ ንፍሮና በግንቦት ሠርግ አለመኖር ፤ ፴፮—፴፱

፯/ የቡሄ ታሪክና ዝርዝር ሐተታ ። ............ ፵—፵፪





www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

በዚህ ለሦስተኛ ጊዜ በወጣው «የትንሣኤ» መጽሔታችን ውስጥ በመጽሔቱ ጀርባ ሠፍረው የሚገኙትን አርእስተ ነገሮች የቃላቱን ፍቺ የትመጣቸውን በታሪክ መልክ፤በቤተ ክርስቲያን በኩል ያላቸውን ታዋቂነት፤ ከሕዝብ ልማድ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ሊደረግ የሚገባውን መሻሻል በዝርዝር በጥልቅ ጥናት አቅርበናል ። ይህንንም ያደረግንበት ምክንያት ፤ ለምን እንደሚከበሩና ምን ዓይነት ታሪካዊ ገዞ እንዳላቸው ለሕዝብ ለማስረዳት ስለአሰብን ነው ።

ስለዚህ ይህ መጽሔት በሕዝብ አእምሮ ዘንድ ሲገላሉ የኖሩና እንዲሁም የሚኖሩ አያሌ ጥያቄዎች እንደሚያብራሩና ስለነዚህም አርእስተ ነገሮች በመጠኑ የሚፈለገውን ያህል ዕውቀት ሊያበረክት እንደሚችል እንተማመናለን ። እንደሚታወቀው ሁሉ በሀገራችን አያሌዎች ከሕዝብ ልማድ ጋር የተወሳሰቡ ባህላትና በዓላት አሉ ፤ ሕዝቡም ያከብራቸዋል ። ለምን እንደሚከበሩ ግን የሚያውቀው በጣም ያነሰ ነው። ስለዚህ እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች ለሕዝብ ማስረዳትና ማብራሪያ መስጠት የቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ተግባሯ ስለሆነ ፤ እነሆ በዚህ መጽሔታችን ውስጥ የነዚህን ነገሮች ዝርዝር ሐተታ ከአስተያየት ጋር አትመን አቅርበናል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅ ዱ ስ ዮ ሐ ን ስ

፩ኛ/ የቃሉ ትርጉም ዮሐንስ ማለት ፍጹም ደስታ ማለት ስለሆነ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለአባቱ ለዘካርያስ ወንድ ልጅ ትወልዳለህ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ፤ እሱም በዋጁ ነጋሪ ሆኖ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረት የአምላካችንን መንገድ አስተካክሉ ፤ ጐድጓዳው ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል ፤ ጠማማውም ይቅና ። ስርጉጡም ሜዳ ይሁን እያለ መንፈሳዊ ደስታን ለምእመናን ያተረፈና እግዚአብሔርና ሕዝብ የሚገናኙበት መንገድ እንዲተካከልና ጥርጊያውም እንዲያምር በቃል ብቻ ሳይሆን በሥራ ገልጾ ያሳየ አዲስ መንፈሳዊ መሪ በመሆኑ አሮጌው ሔዶ አዲሱ ዘመን ሲተካ ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ደስታ የያዘ ከዚህ የበለጠ አስደሳች ነገር ባለመገኘቱ ይህ ቀን የደስታ ቀን ሆኖ በየጊዜው የሚነሣው ትውልድ ሁሉ ሲያከብረው እንዲኖር በመጥምቁ ዮሐንስ ስም ተሰይሞ ተጠራ ።

## ፪ኛ/ የዘመን አቈጣጠር የትመጣው በታሪክ መልክ ፤

የስሙን ትርጓሜና የበዓሉን አከባበር በጥቂቱ ከገለፅን ሁኔታው ከምን እንደመጣና ድርጊቱስ ከምን እንደተገኘ ፤ ከምንስ እንደተወረሰ ይህም ጠቃሚ ግድ ይሆንብናል ። አመጣጡም በመጀመሪያ ጊዜ የእግዚአብሔር ወዳጆች ተብለው ከሚጠሩት ከዕብራውያን ዘንድ ነው እንጂ ሳይታሰብ እንደ እንግዳ ደራሽ በድንገትም እንደ ውኃ ፈሳሽ ሆኖ የተገኘ ድንገተኛ ለውጥ አይደለም ።

ይኸም ራሳቸው እስራኤል በየዓመቱ ዘመናቸውን ይለውጡ የነበር በሎ ስከረም ወር ስለሆነ እኛም ከጥንት ጀምሮ ሕገ ኦሪትን የተቀበልን ፤ በባህላቸው በሥርዓታቸው የበኖን ጥንታውያን ሕዝቦች እንደ መሆናችን መጠን ከቀድሞ ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ በመሆኑ ዘመናችንን በዚሁ በመስከረም ወር በጎ ለውጥ ፤ ስናከብር ቆይተናል ።

በእስክድርያ ከነበረው ጰቶሎሚዎስ ወይም በጥሊሞስ ከተባለው የዘመን አቈጣጠር ጋር ተመሳስሎ እናገኘዋለን ፤ ስለዚህ እንደ ባሕረ ሐሳባችን ወይም እንደ አቡሻክር አቈጣጠር የሔድን እንደ ሆነ ይህንኑ ዘመን የዘመን መለወጫ ወይም አዲስ ዘመን አድርጎት እናገኘዋለን ።

ይሁን እንጂ እኛ ኢትዮጵያውያን አዲስ ዘመን እንዲሆን የፈለግንበት ዋናው ምክንያት ታቹ ውኃ ላዩ ውኃ ሆኖ ዘመድን ከዘመዱ ወገንን ከወገኑ ለይቶት የነበረው የክረምት ወራት አልፎ የተለያየው የሚገናኝበት የራቀው የሚቀርብበት በጠቅላላው ጨለማው ንጉዶ የሰው ልጅ የፀሐይ ብርሃን የሚያገ



www.ethiopianorthodox.org

በት ሙሉ ሕይወት ፍጹም ደስታ የሚገኝበት በመሆኑ አዲስ ዘመን ብለን የዘመን መለወጫ አድርገን ይዘናል ፤ ይህም ዘመን እንደ ባሕረ ሐሳባችን አቈጣጠር ከዚያን ጊዜ ጀምረን ጉዞዋችንን በዚሁ መሥመር ስለቀጠልን ከብዙ አገሮች ጋር በአጽዋማትም ሆነ በበዓላት በማንኛውም ረገድ ለብዙ ጊዜ ሳይለዋወጥ በመቆየቱ እስካሁን ድረስ ይዘነው ቆይተናል ፤ ወደፊትም ይህንኑ ሳን ሌላ እንጥራለን ።

ኢትዮጵያ በአዲሱ ዘመን ብዙ መሻሻልን ስታደርግና ከምዕራባውያን ሥልጣኔ ጋር ማቀራረብ እንደጀመረች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንስ የዘመን አለዋወጥን ከምዕራባውያን የዘመን አቈጣጠር ጋር የማታቀራርብበት ምን ምክንያት አለ ? የሚል ጥያቄ በርከት ባሉት ሰዎች በኩል ሲቀርብ ጥቂቶቹ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ማንም ሰው በክርስቶስ ዘንድ አዲስ ፍጥረት ነው ። አሮጌው ነገር አልፎዋል ። እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል ብሎ በተናገረው መሠረት ሰውም ዘመኑም ማንኛውም ነገር ታደሰ ማለት ስለሆነ ፤ የክርስቶስ ልደት ወዲያው እንደዋለ በቅርብ መሆን ነበረበት እንጂ የክረምቱ ወራት እስኪያልፍ ድረስ መጠበቅ አልነበረበትም የሚል አስተያየታቸውን ሲሰነዝሩ ይሰማሉ ፤ ይህንንም ማለታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለውጥን ፤ መሻሻልን እንደማትወድ አድርገው በመገመታቸው ሁኔታው ጠለቅ አድርጎ የገባቸው አይመስልም ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከቀድሞ ጀምሮ አርቆ አስተዋይ መሪዎችና መንፈስ ጠንካራ የሆኑ ሊቃውንት ስላሏት እውነተኛ ነገር ካልሆነ በቀር ሰው ይውደደን በማለት በሆነ ባልሆነው ነገር ተመሳስሎ መኖርን ስለማይፈልጉ ነው እንጂ ፤ ሊቃውንት ተሰብስበው በነገሩ ተመካክረውበት ፤ ተወያይተውበት መልካም ውጤት የሚያስገኝ ከሆነ የማትስማማበት ምንም ምክንያት እንደሌለ ግልፅ ነው ። ነገር ግን እስካሁን ድረስ ጠቃሚ ነገር ስላላገኘችበት የራሱዋን አቈጣጠር ይዛ ቆይታለች ።

ለመቀራረብ ያልፈለገችበትንም ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን ። ምዕራባውያን አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁለት ጊዜ ለውጠው አሁን ደግሞ ትክክለኛ አይደለም በማለት ቀድሞ ወደነበሩበት ለመመለስ እንደሚፈልጉ በየጊዜው የተነሡ የዘመን አቈጣጠር ሊቃውንት ያስረዳሉ ፤ ችግሩ በዚህ ብቻ ተወስኖ አልቀረም ፤ እኛን በአራቱ አቈጣጠር ፯ ዓመት ያህል ወደኋላ ቀርታችኋል እያሉ ይተቹብናል ፤ እነሱ ደግሞ ቀድሞ የነበሩበትን ፩ ዓመት ለቀው ፲ ዓመት ስለጨመሩበት እንደገና መመለስ አለብን የሚል ስሜት አላቸው ። በየጊዜው የሚለዋወጥ እርግጠኛው የማይታወቅ ከሆነ መለወጡ ምን ይጠቅማል ።



መቀራረቡም ሆነ መለዋወጡ ከጉዳት በቀር የሚሰጠው አንዳች ጥቅም የለም ። በተለይም የግሪክ ቤተ ክርስቲያን የምዕራባውያንን ዘመን አቈጣጠር ተከትላ ስለሔደች ቤተ ክርስቲያኗ ከሁለት ተከፍሏል ። ለምሳሌ ኒዎኔሮሎጂቴ የተባሉት ክፍሎች አዲሱን ካላንደር ሲከተሉ ፖሊዩኤኔሮሎጂቴ የተባሉት ክፍሎች አሮጌውን ካላንደር ይከተላሉ ።

በዚሁ ለውጥ ምክንያት በግሪክ አገር እንኳ አዲሱን ካላንደር አንቀበልም በማለት በስደት ላይ የሚኖሩ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ግልጽ ነው ። በተጨማሪም አጊዎን ኦሮስ ወይንም ማውንት አቶስ በሚባለው ሥፍ የሚገኙ ቍጥራቸው እስከ ፳ የሚደርስ ገዳማት ጥንታዊውን ካላንደር ተከትለው ከመሔዳቸው የተነሣ በጾምም ሆነ በበዓል አከባበር ከእኛ ተባብረው ይገኛሉ ።

ከዚህ ሌላ ደግሞ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ያለው እንኳ ሳይቀር ፖሊዩ ኢሜሮሊጂ በመሆኑ እስካሁን ድረስ የጥንቱን ካላንደር ይዞ ይገኛል ።

ይኸ ብቻ ሳይሆን የእስላቦኒክ በተለይም የሩሲያ ቤተ ክርስቲያንም ያለው በጥንታዊው ካላንደር ነው ። ከላይ የዘረዘርናቸው ሁሉ ከኛ ጋር አንድ ስለሆኑ ዘመናችንን ለውጠን ምዕራባውያንን የምንከተልበት ምንም ምክንያት ያለ አይመስለኝም ። ይሁን እንጂ በ፲፱፻፶፯ ዓ ም በጥር ወር አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ መሪዎች ጉባኤ ፤ በዚህ ሁሉም እንዲተባበርበት በማለት ለብዙ ዘመን ሲያጨቃጭቅ የቆየው ይህ አርእስተ ጉዳይ ተነሥቶ ነበር ። ሆኖም እንደማላባ ወይም ማላባር ወይም እንደ ሕንድ ኦርቶዶክሳውያን ያሉት የምዕራባውያንን ዘመን አቈጣጠር ተከትለው ከምዕራባውያን ጋር ያከብራሉ ። የሶርያም ኦርቶዶክስ ቤክ/ የሕንድ አባት ስለሆነ ፤ እሱም ምዕራብን ተከትሏል ። የግብፅ ኮፕቲኮች ኦርቶዶክሶች ግን እስካሁን ድረስ በጥንቱ ካላንደር ነው የሚጠቀሙት ። ይህም በመሆኑ በመካከል መለያየትን ስለሚያመጣ በእምነት በትምህርት ፤ በሥነ ሥርዓት አንድ ስንሆን በዚህ በዘመን አለዋወጥና በበዓል አከባበር በኩል ምዕራቡን ወይም ምሥራቁን ሁላችንም ተባብረን መያዝ አለብን እንጂ ፤ ለምን እንለያያለን የሚል አሳብ መቅረቡ አልቀረም ። ነገር ግን ሰፋ ያለ ክርክርን በማስከተሉ መጠናት ያስፈልገዋል ተባለ ።

በተጨማሪም ምዕራባውያን ለመለወጥ በሚፈልጉበት ጊዜ አብረን ተመካክረን አስፈላጊውን ነገር ብናደርግ ይሻላል እንጂ እንደገና ወደእነሱ ዘመን



www.ethiopianorthodox.org

ሊለዋወጥ መመለስ የለብንም ። ሁላችንም በያዝነው እንቆይ የሚል ውሳኔ ስለ ተወሰነ ፤ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠርና የበዓል አከባበር ከጥንት ጀምሮ እውነተኛውን መንገድ የተከተለ ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ምስክር አይገኝለትም ።

## ፫ኛ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው የበዐሉ መልክ ፤

መልክ ስንል ዓይነቱን ወይም የገጥታውን ወዘና ማለት ሳይሆን ፤ በቤተ ክርስቲያን በኩል ምን ያህል የአክብሮት መልክ እንደሚደረግለትና የቱን ያህል ተወዳጅነት እንዳለው ለመግለጽ ነው ። ቅዱስ ዮሐንስ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ባየ ጊዜ ፤ እነሆ የእግዚብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድና ስለቤተ ክርስቲያንም ዘለዓለማዊ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ገልጾ ለእምመናን ስላስተማረና በመጨረሻም ራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰፊ ያለ ክብር ሰጥታዋለች ። መታሰቢያውንም አቋቁማለታለች ። ከዚህም የተነሣ በየዓመቱ የዘመን መለወጫ እንዲሆን ውሳኔ ከማስተላለፏም በላይ ፤ በዓላት በየጊዜው የሚከበሩበትና የሚውሉበት ቀኑ ሳይሳሳት መንገዱን ይዞ እንዲራመድና አጽዋማትም የሚገቡበትና የሚፈጸሙበት ዕለቱ ሳይዛነፍ ፤ መልኩን ሳይለቅ ፤ ቀጥታ መሥመሩን ይዞ እንዲጓዝ በባሕረ ሐሳብ ፤ ወይም በአቡሻክር እየተቈጠረ ሲከበር እንዲኖር በሕዝብም ዘንድ እንዲከበር አድርጋለች ።

ይህም በመሆኑ የቅዱስ ዮሐንስ በዓል በየዓመቱ በሚውልበትና በሚከበርበትም ዕለት የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ ፤ ወይም የተማረው ሊቅ ባሕረ ሐሳቡን እያወጣ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ቀን ለምእመናኑ ግልጽ እያደረገ በሚያስተምርበት ጊዜ ፤ ዘቢብ ፤ ዕጣን ፤ ስንዴ እኒህንና እነዚህን የመሳሰሉት ቀርበው ይጸለይባቸዋል ። ይህም የሚፈጸምበት ዋናው ምክንያት በምድር ላይ የተዘራው እህል ፤ የተተከለው አትክልት በረዶ ሳይመታው ፤ አንበጣ ተምች ሳይበላው ፤ ብርድና ድርቅ ሳያገኘው መልካም ፍሬ እንዲያፈራና ብዙም በረከት ለሀገር እንዲያተርፍ በማለት መሆኑ ለማንም አይዘነጋም ።

በፊቱም ሆነ በኋላው በሀገራችን በኩል እስካሁን ድረስ በሙዚቀኛነቱ አንደኛነትን ያልለቀቀ በየጊዜው ከሚነሡት ከዓለም የሙዚቃ ደራሲያንም የአራተኛነትን ደረጃ እንደያዘ የሚነገርለት ቅዱስ ያሬድ በድጓው መጀመሪያ በዘመረለት መዝሙር መታሰቢያው በቆመበት ብቻ ሳይሆን ፤ በመላ ኢትዮጵያ ባሉት አድባራትና ገዳማት ፤ እንዲሁም በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙ ካህናት ማኅሌት ቆመው ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ ዓለም ሳለ የፈጸማቸውን መንፈሳዊ ሥራዎች ሁሉ እያነሱ ሲዘምሩለት ፤ ሲያሸበሽቡለት እንዲውሉና በዓሉንም በታላቅ ደስታ እንዲያከብሩለት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታዛለች ። አክብራም ታስከብርለታለች ። ቅዱስ ዮሐንስም ለጊዜው ምሳሌ ሆና የቆየችው ደብተራ ኦሪት « እንዲሁም ቤተ መቅደስ ከነሥራቸው አልፈው ለዓለምድኅንነት መሥዋዕት ሆኖ የቀረበው መርዓዊሃ ለቤተ ክርስቲያን የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ሥጋና ደም የሚሠዋባት ዘለዓለማዊት የሆነች የወንጌል ቤተ ክርስቲያን የምትቋቋምበትን አዲስ መንገድ ለመጥረግ የደከመ የመንፈስ አርበኛ በመሆኑ ፤ በቤተ ክርስቲያን በኩል የአክብሮት መልክ ሊያገኝ የቻለው ስለዚህ ነው ።

አራቱ ወንጌላውያን በቤተ ክርስቲያን በኩል ምን መልክ ኑሯቸው ነው ? ዘመነ ማቴዎስ ፤ ዘመነ ማርቆስ ፤ ዘመነ ሉቃስ ፤ ዘመነ ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ በማለት ዘመኑን በተራ በስማቸው ተከፋፍለው ይጠራሉ ። ይህስ የሆነበት ምክንያቱ ምንድነው ? የሚል ጥያቄ ይቀርብልን ይሆናል ። መልሱንም ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን ። ለምሳሌ ታማኝ አገልጋይ የሆነ አንድ ሰው የመንግሥት ታሪክና ዜና አሰናጅ ሆኖ ንጉሡ በየመንግሥታቱ እየተዘዋወረ ያደረገውን የአገር ጉብኝት ፤ የተዋዋላቸውንም የውል ሰነዶች ፤ የፈረደውን ፍርድና ለሕዝብም የፈጸማቸውን በጎ ሥራዎች ፤ ለሀገሪቱም ያደረገውን ልማትና ዕድገት በጦር ሜዳም ተዋግቶ ያስገኘውን ድል ፤ እኒህንና እነዚህን የመሳሰሉትን መልካም የሥራ ፍሬዎች በጋዜጣ ፤ በመጽሐት እየገለጠ ሕዝቡ ሁሉ አንብቦ እንዲረዳውና ጠቅላላ ሁኔታውንም በታሪክ መልክ አዘጋጅቶ በየጊዜው ለሚነሣው ትውልድ እንዲተላለፍ ያደረገ እንደሆነ ይህን የመሰለ ቅን አገልግሎት በማበርከቱ ከፍተኛ ደመወዝና ሽልማት ብቻ በማግኘት ሳይወሰን ፤ የማዕርግ ዕድገት እንደሚሰጠው ሁሉ ፤ አራቱ ወንጌላውያንም ለዓለም መድኃኒት ለመሆን የመጣው ክርስቶስ በምድረ እሥራኤል እየተዘዋወረ ያስተማረውን ትምህርት ፤ ያሳየውን ተአምራት ፤ በጠቅላላው የሰጠውን ምሕረትና የደረሰበትን ግፍና መከራ ሁሉ አንድ በአንድ ዘርዝረው ጽፈው በየጊዜው የሚነሡት ምእመናን ሁሉ ሕይወተ ሥጋና ሕይወተ ነፍስ አግኝተው እንዲጠቀሙበት በማለት በታሪክና በትምህርት መልክ አዘጋጅተው ወንጌልን ስላበረከቱና መንፈሳዊ ቅርስም ሆኖ እንዲኖር ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አውርሰው ስላለፉ ፤ ቅን አስተያየት ያላቸው መንፈሳዊ መሪዎችና የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተሰብ





www.ethiopianorthodox.org

ስበው ነገሩን አንድ በአንድ ከተነጋገሩ በኋላ ፤ በድምፅ ብልጫ አጽድቀው ለመልካም ሥራቸው መታሰቢያ እንዲሆንና ስማቸውም ሲጠራበት እንዲኖር ሲሉ ዘመናትን በተራ እየተከፋፈሉ እንዲሾሙ ወስነውላቸዋል ።

በተጨማሪም ገጸ ብእሲ ፤ ገጸ አንበሳ ፤ ገጸ ላህም ፤ ገጸ ንሥር ፤ እየትባሉ አራቱ ወንጌላውያን ይጠራሉ ። ይህስ የመጠሪያ ምልክት ፤ ወይም መለዮ የተሰጣቸው እንዴት ነው ? የሚል አስተያየት ያጋጥመን ይሆናል ። ምክንያምቱን ከዚህ በታች እናቀርባለን ።

ለምሳሌ ፤ ወታደር ወታደር ፤ መሆኑ በሕዝብ ዘንድ ሊታወቅ የሚችለው በጦር ሜዳ ተገኝቶ በመዋጋቱና ሰልፍም በመሰለፉ ፤ ወይንም መዛሪያውን ይዞ በተጠንቀቅ ቆሞ የሚጠብቀውን ሥፍራ በማስከበሩ ብቻ ሳይሆን ፤ ወታደርነቱን ሊያስታውቅለት የሚችለው በራሱ ላይ በሚያደርገው መለዮና በየደረቱ ፤ በየክንዱ በሚለያደርገው ምልክት መሆኑ ግልጥ ነው ። ማቴዎስ ገጸ ብእሲ የተባለው ሰው አምላክ ሆነ ፤ አምላክ ሰው ሆነ ሲል ምሥጢረ ሥጋዌን አጉልቶ ስለጻፈ ነው ። ማርቆስም በግብፅ ይመለኩ የነበሩትን ጣዖታት እንዲጠፉ የወንጌልን ጠቃሚነትና የእግዚአብሔርን አምላክነት እንደ አንበሳ እየጮኸ በመስበክ የጣዖትን ኃይል ሰባብሮ ጥሎ የእግዚአብሔርን ኃይል ስለተካበት ፤ ገጸ አንበሳ ተባለ ። ሉቃስም ቀንድ እያለው የማይዋጋ የላም ተመሳሳይ የሆነው ክርስቶስ ወደ ሚሠዋበት ሥፍራ ተነድቶ ሔደ ። ስለዓለም ተሠዋ እያለ አስተምሮ ብዙ አሕዛብን ስላሳመነ ፤ ገጸ ላህም ተባለ ። « ዮሐንስም ንሥር ወደ ላይ መጥቆ ወጥቶ ቁልቁል የተመለከተ እንደሆነ ዓይኑ የጠራ ስለሆነ ፤ የስናፍጭ ቅንጣት የምታህል የሥጋ ቁራጭ ከመሬት ላይ ብትወድቅ እንኳን ከሱ ልትሠወር አትችልም ። ዮሐንስም ምሥጢረ መለኮትን አምልቶ አስፍቶ ቃል አስቀድሞ ነበረ እግዚአብሔርም ቃል ነበረ ሲል ስለጻፈ ፤ ገጸ ንሥር የሚባል ስም ተሰጠው ።

ስለዚህ ማንኛውም ሁሉ መታወቂያ ምልክት ከሌለው ሊታወቅ እንደማይችል ቀደም ብለን እንደተናገርን ይታወሳል ። አራቱ ወንጌላዊያንም በምእመናን ዘንድ የመታወቂያ ምልክት ሆኖዋቸው እንዲኖር በማለት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህን የመሰለ መንፈሳዊ መለዮ ስለ መልካም አገልግሎታቸው ሸልማቸዋለች ። ይህስ ሁኔታ በየት አገር ተወሰነ ? ወሳኙስ ማነው ? ወደ ኢትዮጵያስ መቼ ? እንዴት ገባ የሚል አስተያየት ሳይገጥመን አይቀርም ። መልሱን በቅደም ተከተል ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን ። በቀድሞ ዘመን የነበሩ የኮከብ ቈጠራ ሊቃውንት ( ወይም አስትሮኖመርስ ) ዘመናትንም ሀገ ወራትን ይከፋፍሉ የነበረ በከዋክብት ስለነበር ይህም ልምድ ረዘም ላለ ጊዜ በሕዝቡ ዘንድ ተጠንቶ ቆይቶ ነበር ። ክርስትና ከተቋቋመ ጀምሮ የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ድሜጥሮስ እስከ ተሾመበት ጊዜ ድረስ የበዓላትና የአጽዋማት አወጣጥና የዘመናትም አከፋፈል መንፈሳውያን በሆኑ ሰዎች ስም የተወሰነ ስላልነበር በ፪፻፲ ዓ/ ም/ ሊቃውንትን በጉባኤ ሰብስቦ በዓላት የሚውሉበትን አፅዋማት የሚገቡበትንና የሚፈጸሙበትን በባሕረ ሐሳብ ደንግጎ ካዘጋጀ በኋላ የኮከብ መቍጠር ለክርስትና እምነት ጠንቅ መሆኑን ስለተረዳ በየዓመቱ በከዋክብት ይከፋፈሉ የነበሩትን ዘመናት በአራቱ ወንጌላውያን እንዲከፋፈሉ የወሰነ እሱ ነው ተብሎ ይታሰባል ፤ ይህ ሁኔታ ግን ወደ ሀገራችን የገባው በአራተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በአብርሃና በአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ከአቡነ አትናቴዎስ ዘንድ ማዕረገ ጵጵስናን ለማምጣት ሔዶ እስክንድርያ ሁለት ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ሢመተጵጵስናን ተቀብሎ ሲመለስ የክርስትናን እምነት ከቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ጋር ይኸንንም ጨምሮ ይዞ የመጣ እሱ ነው እየተባለ በብዙዎች በኩል ይገመታል ።

## እ ን ቍ ጣ ጣ ሽ ።

በሌላ በኩል ደግሞ እንቍጣጣሽ በየዓመቱ ያምጣሽ የተባለው ቃል ከማን እንደተወረሰ ልዩ ልዩ አሳብ ሲሰጥበት እንደቆየ ግልፅ እንጂ የተሠወረ አይደለም ፤ እኛም የተቻለንን ያህል እናቀርባለን ንግሥተ ሳባ በሀገሯ የሚገኘውን ታሪክ ለማስተዋወቅ የሕዝቡንም ሁኔታ ለመግለፅ የሰሎሞንንም ጥበብ በዓይኗ አይታ ለመረዳት የጕብኝትም ለውጥ ለማድረግ ኢየሩሳሌም ሔዳ ጉብኝቱዋን ፈጽማ ስትመለስ ሰሎሞን ሁሉ ነገር ሞልቶ የተትረፈረፈው ሀብታም ንጉሥ ስለነበር በወሰደችለት ወርቅና ሽቱ ለውጥ ብዙ ዕንቍ ለጣጣሽ «ለችግርሽ» ይሁን ብሎ መታሰቢያ ሰጥቶ ሰደ‌ጓት ነበር ። ንጉሡ ሰሎሞን ለእርሱዋ በርከት ያሉ ዕንቍዎች ለገጸ በረከት ሰጥቶ አስደስቶ እንደሰደዳት ከትንሽ እስከ ትልቅ ወሬው በሀገሯ ተሰምቶ ስለነበር ንግሥተ ሳባ አንድ ዓመት ያህል ቆይታ ከመናገሻ ከተማዋ በገባች ጊዜ ወንዱ በሆታ ሴቱ በዕልልታ ሲቀበላት ሕፃናቱ ደግሞ አበባ ፤ ለምለም ቅጠል ይዘው ሰሎሞን ዕንቍ ለጣጣሽ ሰጠሽ በዓመትሽ ፤ እንኳን ደህና መጣሽ እያሉ ስለተቀበሏት ይህ ነገር ልምድ ሆኖ ቀረ ። ይህንንም ልማድ መሠረት በማድረግ ይህ ታላቁ ዓውደ ዓመት በሚውልበት ቀን በየዘመዶቻቸው ቤት እየሔዱ እንቍጣጣሽ በየዓመቱ ያምጣሽ እያሉ የአበባ ገጸ በረከት ይሰጣሉ ። ነገሥታቱ ፤ መኳንንቱ ለልጆቻ





www.ethiopianorthodox.org

ችው ዕንቍ ለጣጣችሁ ይሁን እያሉ ሲሰጡ ድኆች ደግሞ ብርም ፣ ፣ ፍየልም ፣ ልብስም ለጣጣችሁ « ለችግራችሁ » ይሁን እያሉ ይሰጡ ስለነበር ፤ ዛሬም በዘመናችን ያሉት ሕፃናት ለጣጣቸውና ለችግራቸው እንዲያገኙ በማለት አበባ ይዘው ሔደው እንቍጣጣሽ ብለው ያበረክታሉ ። ልጃገረዶችም ተሰብስበው አታሞ እየመቱ ፤ እያጨበጨቡ ፤ እየዘፈኑ አበባ በመስጠት ቤቱን ሁሉ ያዳርሳሉ ። የተቻለውም ለጣጣቸው ለችግራቸው የሚሆን ገንዘብ ይሰጧቸዋል ። ከዚህም የተነሣ ዕንቍ ለጣጣሽ በማለት ፈንታ ከጊዜ ብዛት ለ የተባለው ፊደል ቀርቶ እንቍጣጣሽ ተባለ ፤ እያሉ ብዙ ሰዎች አሳብ ይሰጣሉ ።

ይኸም ሁኔታ ከቀድሞ ጀምሮ ከቤተ መንግሥቱ የመጣ ለመሆኑ አሁንም በጊዜያችን ሕፃናት ወደ ቤተ መንግሥቱ እየሔዱ እንቍጣሽ በማለት አበባ ይሰጡና ከግርማዊ ጃንሆይ እጅ ለችግራቸው የሚሆን የገንዘብ ችሮታ ይደረግላቸዋል ።

## ፬ኛ/ ከሕዝቡ ልማድ ጋር ያለው ግንኙነት ፤

ሕዝቡ የዘመን መለወጫ ከሆነው ከቅዱስ ዮሐንስ በዓል ጋር በልማድ ያለው ግንኙነት በብዙ ረገድ የተለያየ ነው ፤ እምነትን ተመርኩዞ ከሚያከብረው ክፍል ይልቅ ከእምነት ውጭ የሆነውን አሳፋሪ ልማድ ተከትሎ የሚያከብረው ወገን በርክቶ ፤ እንደሚል ይገመታል ። ይሁን እንጂ ልማዱ ከምን ተወረሰ የሚል አስተያየት እንዳለ ግልጽ ነው ። ምክንያቱንም ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን እግዚአብሔር በመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ በሠራው ኃጢአት መፀፀቱን ትቶ በይበልጥ ልቡ ስለደነደነ ዓለምን በጥፋት ውኃ ሲበቀለው ኖኅን ግን ቤተ ሰቡንና በልባቸው የሚሳቡትን ተንቀሳቃሾች በክንፋቸው የሚበሩትን አእዋፍ እንስሳትንና አራዊትን ከጥፋት ውኃ ለዘር አተረፋቸው ። ኖኅም እንዲህ ያለው ጥፋት ከምድር ገጽ ላይ ወዲያው እንደተወገደ ታላቅ በዓል አደረገና ከእንስሳትም ፤ ከአራዊትም ፤ ከአእዋፍም ወገን ልዩ ልዩ መልክ ያላቸውን በዓይነታቸውም ሆነ በቀለማቸው ለዓይን የሚያስደስቱትን መርጦ ለፈጣሪው መስዋዕት አቀረበ ። ከአዝርዕትም መካከል ጥሩ ጥሩ ፍሬዎችን በብዛት ለቅሞ ግማሹን በመቁላት ግማሹንም በመቀቀል ጥቂቶቹንም በማሳረር ረጭቶና በትኖ እንዲሁም የተፈጨውንም ዱቄት ለውሶ ቂጣ ጋግሮ በመጣል በዚህ ሁኔታ የተወደደ መስዋዕት አድርጎ ለአምላኩ ሰጥቷል ይባላል ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የመሥዋዕቱ መዓዛ ስላስደሰተው ከእንግዲህ ወዲህ በልጆችህም ሆነ በምድር ላይ የጥፋት ውኃ አላዘንምም ሲል በራሱ ምሎ ቃል እንደገባለት ይታወሳል ። ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፰ ቍ ፳—፳፪ ። ሙሴም



እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ዕብራውያንን ከበጐቻችሁ መካከል መልክ ያለውን በግ መርጣችሁ እረዱና ሥጋውን ጠብሳችሁ ብሉት ። አታሳድሩት ደሙን ግን በራፋችሁን ለቅልቁት ፤ ቤታችሁን ሁሉ ቀቡት አላቸው ፤ እነሱም ፤ ይኸንን ባደረጉ ጊዜ የታዘዘው በሽታ ወይም መቅሰፍት ይህንን ያላደረጉትን ግብፃውያንን ሲገድል ዕብራውያን ግን ከእንዲህ ያለው መቅሰፍት ነፃ ሆነዋል ። ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፲፪ ቍ ፳ ። ኖኅና ሙሴ ስለበጎ ነገር ያደረጉትን መንፈሳዊ ድርጊት በየጊዜው የተነሣው ትውልድ ወደ መጥፎ ነገር ለውጦ ልዩ ልዩ እንስሳትን እየመረጠ ፤ ለጣዖት ያቀረብ ጀመር ። ይህም ልማድ ቀስ በቀስ ወደ ኢትዮጵያ በየጊዜው ከገቡት ልዩ ልዩ ነገዶች ጋር አብሮ ገባና እስካሁን ድረስ የሚሠራበት ከዚህ የተነሣ ነው ። ሕዝቡም ከበዓሉ ጋር ያለውን የልማድ ግንኙነት እምነትን ተመርኩዞ ሳይሆን ከእምነት ውጭ የሆነውን አሳፋሪ ልማድ ተከትሎ ልዩ ልዩ መልክ ያላቸውን እንስሳት በውድ እየገዛ ለአድባር ለቆሌ ያቀርባል ። የእህልም ዘር እየቆላ ፤ እየቀቀለ ፤ እያሳረረ ይረጫል « ይበትናል » ፤ ቂጣ ጋግሮ ይጥላል ለወንዝ ለተራራ ያሚርታል ፤ ትልቅ ዛፍ እየፈለገ ቅቤ ይቀባል ። ይኸንንም ሁሉ የሚያደርገው ከላይ በተጠቀሱት ነገሮች ላይ መናፍስት ያድሩባቸዋል የሚል ከዘር የወረሰው መጥፎ ልማድ ስላለው ነው ። ይህንን የፈጸምኩ እንደሆን ሀብቱን ያበዛልኛል ከልዩ ልዩ በሽታ ያድነኛል ። ጠላቶቹን አጥፍቶ እኔን በሰላም ይጠብቀኛል ፤ የዘራሁት እህል የወለድኩት ልጅ ይባረክልኛል ፤ ዝናሙን ነፋሱንና የፀሐዩን ብርሃን በየወቅቱ ይሰጠኛል እያለ ተስፋ በማድረግ ያምንበታል ። ድንቁርና ያጠቃው ሕዝብ ከበዓሉ ጋር የልማድ ግንኙነት የሚያደርገው ይህን በመሰለ በአሳዛኝ ሁኔታ ነው ።

በሌላም በኩል ሕዝቡ የመንፈሳዊውን ዓላማ ለቆ ለመናፍስት መንፈሱን እያስገዛ በውድ ገንዘብ ልዩ ልዩ መልክ ያላቸውን ዶሮ ፤ በግ ፤ ኮርማ ገዝቶ እየረደ ከገንዘቡም ፤ ከፈጣሪ ወም ሳይሆን ሕይወቱን ጊዜ ከማይለውጠው አደጋ ላይ ይጥለዋል ። ከሚሰጠው አገልግሎት ይልቅ የሚያመጣው ጉዳት ከፍ ያለ ነው የሚባለው ከዚህ የተነሣ ነው ።

## ፭ኛ ፤ ጥቅሙና ጉዳቱ ።

የሚሰጠው ጥቅም ፤ ጥቅሙስ በምን በምንድነው የሚል ጥያቄ መቅረቡ አይቀርም ። ሁኔታው ይህ ነው ። የኢትዮጵያም ሕዝብ የዘመን መለወጫ ከሆነው ከቅዱስ ዮሐንስ በዓል ጋር ሰፋ ያለ ጥቅም ስላለው በየዓመቱ በታላቅ ናፍቆት ሲጠባበቀው ይቆይና በደረሰም ጊዜ የሀብቱ ምጣኔ በፈቀደለት መጠን ከልብ ሲያከብረው ኑሯል ፣ ወደፊትም ሲያከብረው ይኖራል ።



www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳን ዘመን መለወጫ በየሀገሩ በባሕልና በወግ የተለየየ ቢሆንም በሀገራችን ግን እስካሁን ድረስ በሕዝብ በኩል ያለው የሕዝብ ባሕል እምብዛም የለቀቀ አይመስልም ።

ይህንን ማለታችን የምዕራባውያንን ሥልጣኔ የተከተሉ ዘመናውያን የሆኑ ኢትዮጵያውያን የስጦታ ልውውጥ የሚያደርጉት በርከት ያሉ የውጭ ሀገር መጠጦችን እየገዙ በመገባበዝ ፤ ልዩ ልዩ የሸቀጥ ዕቃዎችን በመግዛት ፤ ሲኒማ ፤ ትያትር በማየት ፤ በደመነስ እኒህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ተግባሮች እየፈጸሙ በዓሉን በደስታ ይጠቀሙበታል ። ምንም እንኳን ይህ ሁኔታ በአዲሱ ትውልድ ዘንድ ጠቃሚ መስሎ ቢገመትም አልፎ አልፎ እንጂ እምብዛም አይደለም ፤ በብዙዎች በኩል የሚሰጠው ጥቅም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ከሚደረገው ጸሎትና ምስጋና ሌላ በየቤቱ ዳቦ በመጋገር ፤ ጠላ በመጥመቅ ፤ እንግጫ በመጐዝጐዝ ፤ ለምለም አበባ በቄጠማ እየጐነጐኑ ከምሰሶ ላይ በማሠር ፤ በበርጩማ በጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ ዘመድ በመጠየቅ ፤ ቤተ ሰብን በመሰብሰብና ጐረቤትና ጐረቤት በመጠራራት ፤ አብሮ በመብላትና በመጠጣት ፤ ብሔራዊ ዘፈን በመዝፈን ፤ ልዩ ልዩ ጫወታ በመጫወት ይጠቀሙበታል ።

እንግዲህ በዓሉ ለሕዝብ ከሚሰጠው ጥቅም ጋር ሕዝቡም ለበዓሉ ከሚያቀርበው ደስታ ጋር የተዛመደ በመሆኑ ብሔራዊ ስሜትን ሳይለቅ ሞቆና ደምቆ ተወዳጅነትን አግኝቶ ፤ ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ጥቅም ለሕዝብ በመስጠቱና በየዓመቱም አዲስ የሥራ ለውጥን በማስገኘቱ ጥቅሙ በሕዝቡ ዘንድ ጐላ ብሎ ይታያል ።

## ፯ኛ ፤ የሚያመጣው ጉዳት ።

ሕዝቡ ሁሉ ባለማመዛዘን ዓመት ሙሉ ሲያጠራቅም ይቆይና ከልክ ያለፈ ድግስ እየደገሰ በየሱቁ የሚገኙትን ሸቀጦች እያነሣና የልብስ ዓይነቶችም አማርጦ እየገዛ በዓሉን ለማክበር ከአቅሙ በላይ እየተግደረደረ ከጉዳት ላይ ይወድቃል ። ደሞዝተኛም የሆነ ለአንድ ወር እንዲሆነው ተወስኖ በተሰጠውም ደመወዙ የሆነ ያልሆነውን ይገዛና ለ፴ ቀን የሚበቃውን የድካሙን ዋጋ በአንድ ቀን ጨርሶ ከታላቅ የችግር አዘቅት ውስጥ ይወድቃል ። ችግርም ሲፀናበት የሚቀጥለውን ወር ደመወዙን ይበደርና ሁልጊዜ ከችግር ሳይወጣ ተበዳሪ ሆኖ ይኖራል ። ባልና ሚስትም ዓመት ሙሉ በስምምነት ይቆዩና በዓሉ በደረሰ ጊዜ ሚስቲቱ ይህንን ግዛልኝ ፤ ባልየውም ገንዘብ የለኝም በመባባል እስከ ፍቺ ይደርሳሉ ።

በጠቅላላው በቤተ ሰቡ ሁሉ ይህን የመሰለ ጭቅጭቅ ስለሚፈጠር ፤ እንዲህ ያለውም ድርጊት የሞራልን ውድቀት ከማስፋፋቱም በላይ ታላቅ የኢኮኖሚም መቃወስ ስለሚያስከትል በሀገሩም ፤ በሕዝቡም ላይ ከፍ ያለጉዳት ሊያመጣ ይችላል ።



## ፰ኛ ፤ መ ሻ ሻ ል ።

ለመሻሻልም ሆነ ከመጥፎ ጠባይም ለመታረም የሚቻለው በትምህርት ነው ፤ ትምህርት ለሁሉ ካልተዳረሰ ግን መሻሻልም ፤ መታረምም እንደማይገኝ ግልፅ ነው ። የሰው ልጅም ተምሮ ካላወቀ በቀር በተፈጥሮ ዕውቀት ብቻ የሚራመድ ከሆነ ምንም ያህል ከእንስሳ ባለመሻሉ ጥቅሙንና ጉዳቱን ሊያውቅ ስለማይችል የነገሩትን ሁሉ አሜን ብሎ እየተቀበለ አልሚውን በመተው አጥፊውን ተከትሎ ይጓዛል ። ለመረጃም ይሆነን ዘንድ የተማሩ ሕዝቦች ሀብታቸውንም ሆነ ጊዜያቸውን እየሠው በሽታ የሚጠፋበትን ፤ ድንቁርና የሚወገድበትን ዘዴ እየፈለጉ ለሀገራቸው ፤ ለወገናቸው ልዩ ልዩ መድኃኒት እየፈለሰፉ ለራሳቸውም ለሌላውም ሕይወት ለማስገኘት ይጥራሉ ፤ ለማሻሻልም ይደክማሉ ።

ትምህርት ያልተዳረሳቸውና መሐይምንነት ያጠቃቸው ሕዝቦች ግን አልሚው አጥፊ አጥፊው አልሚ ስለሚመስላቸው ጠቃሚው ጐጂ እየመሰለ ስለሚገምታቸው ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌላውም መሰናክል ሆነው ይኖራሉ ። ይህም ማለት ሕዝብ በሚተላለፍበት አውራ መንገድና መንታ በሆነ ጐዳና ላይ ቂጣ ቆሎ በመጣል ፤ ዶሮ ገድሎ በመወርወር ለወገኖቻቸው ደንቃራ እየሆኑ ከልዩ ልዩ በሽታ ላይ እንዲወድቁ ይጥራሉ ፤ ይህንንም ማድረጋቸው የራሳቸው በሽታ ወደ ሌላው ተላልፎ እንዲገል በማሰብ ነው ። ይሁን እንጂ በሽታው እነሱን መልሶ ይጐዳቸዋል እንጂ ሌላውን እንደማይጐዳ የታወቀ ነው ።

ይህ ሁኔታ ሊሻሻል የሚችለው ትምህርት ለሁሉም የተዳረሰ እንደሆነ ነው ፤ ካልተዳረሰ ግን ድርጊቱ እየቀጠለ ከመሔድ በቀር መሻሻል አይኖርም ፤ እንዲሻሻልም ከተፈለገ የተማሩት ክፍሎች ያልተማሩትን በተቻላቸው መጠን ማስተማር ይኖርባቸዋል ። በተለይም ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ኑሮ እያሻሻለ ልዩ ልዩ የሆነ የአምልኮተ ጣዖትን ርዝራዥ ከሰው አእምሮ ላይ ነቅሎ ጥሎ በሥፍራው አምልኮተ እግዚአብሔርን ተክቶ በሕዝብ ላይ መስማማትንና መግባባትን የሚፈጥር መሆኑን ማስተማር ይኖርባታል ። ይህም ከሆነ ለብዙ ዘመን ይሠራበት የነበረ መጥፎ ሥራ ሁሉ ከንጹ ምድር ተወግዶ የሁሉም ኑሮ እንደሚሻሻልና መልክም ለውጥ እንደሚገኝ ይታመንበታል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፫ኛ ፤ መደምደሚያ ።

ከአንድ እስከ ሰባት ያሉትን አርእስተ ጉዳዮች ይዞታቸውን ብቻ ሳይሆን አግባባቸውንም በየክፍላቸው ገልጠናል ፤ የዘመን መለወጫ የሆነው የቅዱስ ዮሐንስ በዓል አከባበር በኢትዮጵያ ረዘም ላለ ጊዜ የቆየና ጥንታዊነት ያለው ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ባህል አስተባብሮ የያዘ ከመሆኑም በላይ መልኩን ሳይለውጥ ፤ እርምጃውን ሳያቋርጥ እስካሁን ድረስ አለ ። ወደፊትም መልኩን ሳይለውጥ ይኖራል እንጂ ለውጥ አያሻም ። አባቶቻችንም ሲያከብሩት የኖሩት ከፍ ያለ ዋጋን ስላገኙበት ብቻ ሳይሆን በጎ ተግባርን የተመረኰዘ ሆኖ ሥጋዊ ጥቅምንም ሆነ መንፈሳዊ በረከትን እንደሚሰጣቸው በመተማመን ይሠሩት ስለነበረ ነው ። ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ከቀድሞ ጀምሮ ከእንዲህ ያለው ዓላማ ውጭ ሆኖ ለመኖር የሚሻ እንዳልነበረ የተሠወረ አይደለም ። ይህም በመሆኑ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚነጋገሩትንና በየጠቅላይ ግዛት ተራርቀው ያሉትን የኢትዮጵያን ኑዋሪዎች ሁሉ አስማምቶ እያገናኘ በዝምድና ሲያስተማሥር ለረጅም ጊዜ የኖረ የትልቁንም የትንሹንም ስሜት እየቀሰቀሰና መንፈሳዊ ደስታንም እየሰጠ የቆየ ብሔራዊ በዓል ነው ። ይህንንም የመሰለ መወደድ በየዓመቱ ይዞ ስለሚመጣ በዓሉ ከሕዝቡ ደም ጋር ሥርዖ የኖረና ከአእምሮውም ጋር አብሮ በቀል ሆኖ ያደገ በመሆኑ በአንደኛ ክፍል እንደዘረዘርነው ሁሉ ምንጊዜም ቢሆን ለውጥ ይደረግበታል ተብሎ አይታሰብበትም በዚሁ እንደቀጠለ እንደሚኖር አይጠረጠርም ይልቁንም ለውጥ የሚያሻው የአምልኮተ ጣዖትን ርዝራዥ ይዞ የቆየው አሳፋሪ የሆነው ልማድ መሆን አለበት ።

ይሁን እንጂ በቀድሞ ዘመን የሚኖሩ እምነት የሌላቸው ሕዝቦች በፍጥረት መናፍስት ማመን ይወዱ እንደነበር ያለፈው ታሪካቸው ቢነግረንም ከእንዲህ ያለው ስሕተት ላይ ሊወድቁ የቻሉት ትምህርት ስለሌላቸውና በዓይናቸውም የሚያዩት ግዙፍ አምላክ ይፈልጉ ስለነበር እራሳቸው በሰራቸውና በእንስሳትም ፤ ያለፉትም አባቶቻቸው ሲያመልኩት የነበረውን ማምለክ ግድ ስለሆነባቸው ነው ። ከብዙ ዘመን በኋላ ግን ትምህርት ስለተስፋፋና በአምልኮተ ጣዖትም ፈንታ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለተተካበት ሁኔታው በዐዋቂዎች ዘንድ እንደምናምን ነገር የእተቀጠረ ተናቀ ።



ከዚህም የተነሣ አምልኮተ እግዚአብሔር የጥንቱን አምልኮተ ባዕድ ከነሥራው ሰርዞ አቸናፊ ሆኖ በብዙ ሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን ስላገኘ ከእንስሳት ደም ይልቅ የክርስቶስ ደም መድኀን መሆኑ በሥራ ተረጋገጠ ።

ከዚህም የተነሣ የክርስትና እምነት በዓለም ከተቋቋመ ወዲህ በሰዎች ልጆች መካከል የነበረውን የጥላቻ ጠንቅ አጥፍቶ በእያንዳንዱ ሰውና በቤተ ሰብም ዘንድ ሰላምንና መግባባትን ሊያስገኝ ስለቻለ ልማድን እናሸንፍ እንጂ ልማድ አያሸንፈን ።

ከአለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# ጾ መ ገ ሃ ድ

## ፩/ ስለገሐድ ጾም ።

ገሐድ ማለት በዓርብና በረቡዕ ፋንታ ፤ ወይም ምትክ የሚጾም ጾም ነው። አባቶቻችን ሐዋርያት የልደትና የጥምቀት በዓላት ዓርብና ረቡዕ ቀን በዋሉ ጊዜ እንደመዋዕለ ፋሲካ በመንፈቀ ሌሊት እንዲገደፍ እንጂ እንደ ሌላው ጊዜ እንዳይጾም ሥርዓት ሠርተዋል ። እንዲህ ማድረጋቸው ሁለቱም በዓላት በጣም የተከበሩና የገነኑ በመሆናቸው ።

የሁለቱን በዓል ትልቅነት አባቶች በምሳሌ ሲያስረዱ ሰሞን ሠርቶ ለስ ንበት ፤ ዓመት ለፍቶ ለልደት ይላሉ ። ስለ ጥምቀትም «ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ» በማለት ይናገራሉ ።

እነዚህ በዓላት በእንዲህ ያለ ሁናቴ የተከበሩ ገናኖች ስለሆኑ ፤ እንዳይ ጾሙ በመደረጉ የቀደሙ የቤተ ክርስቲያን መምህራን በዓላችን መንፈሳዊ ሥራ የተለየው እንደ አይሁድ በዓላት ለዚህ ዓለም ተድላ ደስታ ፤ ለመብልና ለመጠጥ ብቻ የተዘጋጀ እንዳይሆን መንፈሳዊነትን ደርቦ የያዘ ሆኖ የጾምና የበዓል ማክበር ጉዳዮች ተባብረው እንዲፈጸሙ ከልደትና ከጥምቀት አስቀድሞ ያሉት ዕለታት እንዲጾሙ አዘዙ ። ስለዚህ እነዚህን ሁለት የጽድቅ ምግባራት ፤ በዓል ማክበርንና ጾም መጾምን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ሠርታዋለች ። ነገር ግን ይህ በዓል እሑድና ሰኞ የዋለ እንደሆነ ሰንበታትን መጾም ስለማይገባ ሰኞ ቢውል እሑድን ፤ እሑድ ቢውል ቅዳሜን የውሎ ጾሙ ቀርቶ በሁዳዴ (፵) ጾም የሚበላውን ጥሉል ያልሆነውን ምግብ መመገብ ብቻ ይበቃል ።

ይህ ጾምም ሲጾም ሕዝባዊ ቢሆን እስከ ፱ ሰዓት ፤ በልደትና በጥምቀት ቀን ስለበዓሉ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል የሚያስቡና ቀድሰው የሚያቆርቡ ካህ ናት (ቀሳውስት ና ዲያቆናት) ቢሆኑ ቀን ሞያቸውን ከመጾማቸው በላይ ፤ እስከ መንፈቀ ሌሊት በጾም ቆይተው ሥጋውንና ደሙን ማቀበልና መቀበል አለባቸው ።

ከዚህም የገናን ገሐድ የተዋሕዶና የጸጋ ሃይማኖት መለያ ስለሚያደርጉት የተዋሕዶ ሃይማኖት ወገኖች በዘመነ ዮሐንስ ልደትን በታኅሣሥ ፳፰ ስለሚ ያከብሩ ፤ አንድ በጸጋ ሃይማኖት የሚያምን ወደ ተዋሕዶ ተመልሶ በ፳፰ ከበላ በኋላ ፤ ተዋሕዶችን እንግዲህማ ተዋሐድን በገሐድ በላሁላችሁ ብሎ ተናገራቸው ይባላል ።



## በዓለ ልደትን በታኅሣሥ ፳፱ ስለማክበር

ከሮም ነገሥታት አብዛኛዎቹ ራሳቸውን በታሪክ የሚያሳውቁበት አንዳ ንድ ምክንያት ይፈጥሩ ነበር ። ከነዚህም ውስጥ ሕርቃል ከዓቢይ ጾም የመጀ መሪያውን ሱባኤ እንደ ዓወጀ ፤ ዩስጣትያኖስ የሚባለውም የሮም ንጉሥ ለም ሥራቅና ለምዕራብ ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉ የልደትን በዓል ካኑን በሚባለው ወር በ፲፩ ቀን ይኸውም ታኅሣሥ ፳፱ ቀን መሆኑ ነው እንዲከበር ጻፈ ። በየዓ መቱ በዚህ ቀን ለማክበር የማይስማሙለት ቢሆን ፤ ሠግር በሆነ ጊዜ ማለት ጳጕሜን ስድስት ስትሆን ለማክበር ከብዙ ክርክር በኋላ ተስማሙ ። የተስማ ሙበትም ምክንያት ፤ ጌታችን በማኅፀነ ድንግል የቆየው ዘጠኝ ወር ካምስት ቀን ነውና የጳጕሜ ስድስት መሆን ዘጠኝ ወር ከስድስት ቀን እንዳያደርገው በቍጥሩ ለመጠንቀቅ ነው በማለት ነው ። ይህንም ዜና ምእመናን ወዓላውያን የሚባለው መጽሐፍ በግእዙ እንደሚከተለው ጽፎት ይገኛል ።

«ኃምስ ጾታ እስመ መብዝኅቶሙ ለነገሥተ ሮም ያመጽኡ ፈጠራ ፤ ከመ ይትዐወቁ ባቲ ወእምኔሆሙ ሕርቃል አጽርዓ ጾመ ዛቲ ፤ ሱባኤ ቀዳማይ እምነ ጾም ወፈትሐሙ ባቲ ወዩስጣትያኖስኒ ንጉሥ ጸሐፈ ኀበ ኵሎሙ ኤጲስ ቆጶሳት ዘምሥራቅ ፤ ወዘምዕራብ ከመ ያብዕሉ በዓለ ልደት ስቡሕ አመ ፲ወ፩ ለወርኀ ካኑን ዘውእቱ ፤ አመ ፳ወ፱ ለወርኀ ታኅሣሥ ወሶበ ኢተከሀሎሙ ተሰ ናእዎ በዝንቱ ተሰነዓው ምስሌሁ በዓመተ ሠግር ባሕቲቱ ወኮነ ጋዕዝ በእንቲአሃ በማለት ጽፎታል ። »

ይህንንም የሮም ንጉሥ ዮስጣትያኖስ ራሱን ዝነኛ ለማድረግ ብሎ በፈ ጠራ እንዲከበር ያደረገውን በዓል ደጋጎቹ የኢትዮጵያ ሊቃውንቶች የጸጋና ፤ የቅብዓት ፤ የተዋሕዶ ፤ ሃይማኖት ፤ መለያ ምልክት አድርገውት ይገኛሉ ። በዚህም የተነሣ ፤ እገሌ በዘመነ ዮሐንስ ፳፰ ታኅሣሥን ይጾማልና ጸጋ ፤ ወይም ቅብዓት ነው በማለት ሲነቅፉት ፤ የጸጋና የቅብዓት ወገኖች ደግሞ ተዋሕዶዎችን በገሐድ ይበላሉ እያሉ ሲያሽሟጥጧቸው ይገኛሉ ።

ይህንንም ለማስረዳት ያንድ ሊቅ ታሪክ እጽፋለሁ ። ባንኮበር አንድ የደ ብር አለቃ የነበሩ ታላቅ የተዋሕዶ ሊቅ ነበሩ ። ካገሩ ውስጥ በ፳፰ አንገድ ጥም የሚሉ የጸጋ ሃይማኖትን የሚከተሉ ብዙዎች ስለነበሩ ፤ የገና (የልደት) በዓል በ፳፰ ቀን በሚከበርበት ጊዜ እነዚህ ጸጋ የሚባሉት የመንግሥቱን ዓዋጅ በመፍራት ከቤተ ክርስቲያን ካስቀደሱ በኋላ ፤ በየቤታቸው ተደብቀው ይጾማሉ እየተባሉ ይታሙ ነበርና ፤ እኚህ ትልቁ የተዋሕዶ ሊቅ ቅዳሴ ተቀ ድሶ ሕዝቡ ወደየቤቱ ለመሔድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ፤ ከቤተ ክርስቲያኑ በር



www.ethiopianorthodox.org

# ሰሙነ ሕማማት

በመላው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት በተለይም በጽቱ አህጉር በሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትም የአገልግሎቱ አፈጻጸም እንደ የሀገሩ ባህል የተለያየ መልክ ቢኖረውም የክርስቶስ መከራ መስቀል መታሰቢያ የሆነውን ሰሙነ ሕማማት በየዓመቱ ማክበር ለክርስቲያኖች ሁሉ የተለመደ ቀዋሚ ሕግ ነው ። በግሪክና በሩሲያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና በመላውም የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ከፍ ባለ ሁኔታ ይከበራል ። ነገር ግን እንደጊዜው ሁኔታ እየተሻሻለ የአገልግሎቱ ብዛት በሕዝበ ክርስቲያን ላይ ከባድ ሸክምን እንዳያስከትል በማሰብ በሊቃውንት እየተጠና በወንጌል ወይም በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ የክርስቶስን ሕማሙን ሞቱን ጠቅላላ ነገረ መስቀሉን ከሚያስታውሰው ታሪክ በቀር ፤ ልዩ ልዩ የሊቃውንት መጻሕፍትና ድርሳናት ከገድልና የታምራት መጻሕፍት አብዛኛዎቹ በተለይ ቤተ መጻሕፍት ተቋቁሞላቸው በዚያው እንዲነበቡ ማድረግ ግዴታ ሆኗል ።

ግብረ ሕማማት የተባለው መጽሐፍ የክርስቶስን ሕማሙን ሞቱን በጠቅላላ ነገረ መስቀሉን በነቢያት የተነገረውን ፤ በወንጌል የተጻፈውን ፤ በሊቃውንትም የተተረጐመውን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ስለሆነ ከሆሣዕና እሑድ ዋዜማ ጀምሮ እስከ ዕለተ ዓርብ በቤተ ክርስቲያን ሲነበብ ይሰነብታል ። ከግብረ ሕማማቱም ንባብ ጋር አብረው የሚጓዙ ልዩ ልዩ ድርሳትናት እንደ ግጥም ያሉ የሚነበቡና የሚዜሙም ብዙ ዓይነት ድርሰቶች ( አርኬዎች ) አሉ ። በተለይም መዝሙረ ዳዊት አንድ በአንድ በተራ እየታደለ ይነበባል ። ኪርያላይሶን ፤ (አቤቱ ማረን) እየተባለና ሌሎችንም የተቀደሱ ቃላት ልዩ ልዩ አስማተ አምላክ በመጥራት የብዙ ጊዜ ስግደት አለ ። ይህም ሁሉ አብዛኛው የሚፈጸመው በካህናቱ አማካይነት ነው በሰሙነ ሕማማት ሰው ቢሞት ጸሎተ ፍትሐት አይደርስም ፤ እግዚአብሔር ይፍታሕ የማለትም የኑዛዜ ቃል አይሰጥም ። ይኸም በአራት ድኅነት የለም ነበር ድኅነት የተገኘው በክርስቶስ ስቅለት ነው ፤ ለማለት ሲባል በዚህ ሳምንት ጸሎተ ፍትሐትም ሆነ እግዚአብሔር ይፍታሕ የማለት የጸሎት የመጨረሻው ቃል አይሰጥም ።



# በሕዝብ ዘንድ ያለው ታዋቂነት

አገልግሎቱ የሚከናወነው አብዛኛውን ጊዜ በካህናቱ ቢሆንም በተለይ ምእመናኑም አንዳንድ ጊዜ ተካፋይ የሚሆኑበት ሰዓት አለ ። በተለይም በዕለተ ዓርብ ከሰዓት በኋላ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት በሕዝብ ( በምእመናን ) ይመላሉ ። ሕዝቡም ሁሉ እንደ ልማድ ሆኖ በሰሙነ ሕማማት የፈጸሙትን ኃጢአት በመናዘዝ በወይራ ቅጠል ቀንበጥ ( እየተጠበጠቡ ) የንስሐ ስግደት እየተቀበሉ እንደ ኃጢአቱ ማነስና መብዛት እየተመዘነ አርባም ሃምሳም ጊዜ ይሰግዳሉ ። ይህም የወይራው ጥብጠባ የክርስቶስን ግርፋት የሚያመለክት ምሳሌያዊ ዝክረ ነገር ነው ።

በዚሁ ዕለት ሕፃናቱ ደግሞ በተለይ እንደ ልማድ አድርገው የያዙት ሙሻ ሙሾ የሚሉት ልማድ አለ ። ሆኖም አልፎ አልፎ በበጌምድር ሰሜንና በጐጃም ጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ ከሚገኙት አውራጃዎች በተለይ በአንዳንዶቹ የሚፈጸም እንጂ የመላውን የኢትዮጵያ ምእመናን የሚያጠቃልል ብሔራዊ ባህል ባለመሆኑና ከክርስቶስም ነገረ ሕማማተ መስቀል ጋር የአለው ግንኙነት ጐልቶ የሚታይ ባለመሆኑ ምክንያት ይህን ሙሻ ሙሾ የተባለውን ልማደ ሕፃናት ብዙ ሐተታ ልንሰጥበት የሚያስፈልግ መስሎ አይታይም ። በአጭሩ ለመረዳት ቢፈለግ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ በጻፉት ማኅበራዊ ኑሮ በኢትዮጵያ በተሰኘው መጽሐፋቸው ከገጽ ፵፫ እስከ ፵፮ ባለው ክፍል መመልከት ይቻላል ።

# ሊሻሻል የሚገባው

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊት ( ቀዳማዊት ) እንደመሆኗ መጠን አያሌ የታሪክ ቅርሶች አሏት ። በታሪክ መጻሕፍትም ብዛት የበለጸገች ናት ። ባህልና ሥርዓቷም የተቀደሰና የተሟላ ስለሆነ ምንም ያህል የተውሶ ባህልና ሥርዓት አያስፈልጋትም ።

ዳሩ ግን በሕዝበ ክርስቲያን በተለይም በወጣቱ (በአዲሱ) ትውልድ ላይ የአገልግሎትን ሕግና ሥርዓት ስለማክበድ ጉዳይ ልታሻሽለው የሚገባት ብዙ ነገር አለ ።



www.ethiopianorthodox.org

በማርገጃው ላይ በግ አሳርደው አሽከሮቻቸውን እያ ጠበሱ እሳቸው ፈንዜያቸውን ታጥቀው ከቤተ ክርስቲያን የሚወጣውን ሁሉ ትበላ እንደሁ ናብላ አለዚያ በፈንዜ አወራርድኻለሁ በማለት እያስፈራሩ በግድ ሲያበሉ ፤ ከተገዳጆቹ አንዱ እገሌ ብሎ ስማቸውን ጠርቶ ለኛ እልክብለህ እዚህ እሜዳ ላይ ስትጠብስ ምኝ ያደብንሃል አላቸው ይባላል ።

ይህንንም ስንክሳር የሚባለው የታሪክ መጽሐፍ የልደት በዓል በጣም ታላቅ ስለሆነ ፤ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ሁለት ቀን እንዲከበር ተስማሙ። ልደት የተደረገው ሌሊት ስለሆነ ፤ ወደኋላ ያለው መዓልት ፳፰ ሲሆን ፤ ጳጉሜን ስድስት በሆነ ጊዜ ሁለቱም ቀን ይከበር እያለ ይጽፋል ። ይህንም በታኅሣሥ ፳፱ ስንክሳር ተመልከት።በ፳፰ም የሚጽፈው የልደትን ታሪክ ነው ።

# አ ስ ተ ያ የ ት

ይኸ ነገር የትመጣውንና የታሪኩን አመሠራረት ለማወቅ ያህል አተት ነው እንጂ ፤ የልደት በዓል ብቻ የሚዘዋወርበት ግዝረቱ ፤ ጥምቀቱ ፤ በታውን የማይለቅበት ምን በቂ አስረጂ ሊኖረው ይችላል ? ይኸ ሁናቴ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የማይደገፍ ለመንታረኪያ የኛ አባቶች ብቻ የፈጠሩት መስሎ ስለሚታይ ፤ በያሙቱ ልደት በ፳፱ ቀን ብቻ ቢሆን መልካም ስለሆነ ፤ ሁላችን እናስብበት ።

## ፪ኛ ጾ መ ሕ ር ቃ ል

ጾመ ሕርቃል ማለት የሕርቃል ጾም ማለት ነው ። ምክንያቱም ሕርቃል በሚባለው የቢዛንቲዳን ንጉሥ የተሰየመ ነው ። እርሱም አይሁድን ስላጠፋ በእግዚአብሔር ዘንድ በደል ሆኖ እንዳይቆጠርበት ክርስቲያኖች የጾሙለት ጾም ማለት ነው ። በዚያ ዘመን አይሁድ ፎቃ በሚባለው ጉሣ ኃይል በምእመናን ላይ የክርስቶስን ስም እንዳይጠሩ ስለተቃወሙዋቸው ፤ ክርስቲያኖቹ አይሁድን በጦር ኃይል እንዲያስታግስላቸውና ፎቃን እንዲያጠፋላቸው ሕርቃልን ጠየቁ ። እርሱም በክርስቶስ ያመነ የክርስቲያንን ሕግ የሚፈራ ነበርና በክርስቲያን ሃይማኖት ሰው የገደለ እስከ እድሜው ፍጻሜ መጾም አለበት የሚል ሕግ አለ ትላላችሁ ። እኔ ለመጾም አልችልም ። እንደምን ይሆናል የሚል መልስ ሰሰጣቸው ፤ በዕድሜህ ልክ ተገምቶ እኛ ክርስቲያን የተባልን ሁሉ ተካፍለን እንጾምልኻለን ብለው ቃል ኪዳን ገቡለት ። እሱም አይሁድን ሊያጠፋላቸው ከማለላቸው በኋላ ፤ ከአይሁድ ወገን ብዙ ሰውና ፎቃን ገድሎ



ጸቡን ካስታገሠ ወዲያ ፡ የዕድሜው ተረፍ ተገምቶ በዚያን ጊዜ ለነበሩ ክርስቲያኖች ቢካፈሉት አምስት አምስት ዕለታት ደርሱቸዋል ። ይህንም ጾመ አስተሥርእዮ ብለው ጾሙውታል ።

ይህ ነገር ሲያያዝ ሠለስቱ ምዕት አርዮስን አውግዘው ሃይማኖትን አቅንተው በሚለያዩበት ጊዜ ፤ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ሲደነግጉ ሕማማትን ከጾመ ፵ ጋር እንደመቀላቀላቸው ፤ ይህንንም የኋላ ሊቃውንት ስምንተኛ ሱባኤ ሁኖ እንዲጾም አዘዋል ። ይኸውም ዜና ምእመናን ወዓላውያን በሚባለው መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል ።

እንዲህ ማድረጋቸውም ፩ኛ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ተጋድሎ ላደረገው ንጉሥ ሥርየት ለመለመን ምእመናን ያደረጉት ሱባኤ የጾሙት ጾም መታሰቢያው በምእመናን ትውልድ ዘንድ እንዳይዘነጋ ማስታወሻ ሆኖ ሲነገር እንዲኖር ለማድረግ ፤

፪/ ሕርቃል በዚያን ዘመን በግብፃውያን ላይ የማዘዝ ሥልጣን ሳይኖረው የሮምና የእስክንድርያ ሊቃነጳጳሳት በመካከላቸው ፍቅር መሥርተው አንዱ የደነገገውን ሕግ ሌላው እንዲቀበል ተስማምተው ስለነበረ ፤ በዚህ ወራት የሮሙ ንጉሥ ታሪኩን ለማሳወቅም ሆነ ዝናውን ለማጋነን ይህ የጾመ አርብዓ ተቀዳሚ ሱባኤ እንዲጾም ስለአዘዘ ፤ ስለሮሙ ሊቀ ጳጳሳት ፍቅር የእስክንድርያውም ሊቀ ጳጳሳት ተቀብሎ እንዲጾም አድርጎት ነበርና የሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳት ቀድሞ የነበራቸው ፍቅር ማስታወሻ እንዲሆን ወስነውታል ።

፫ኛ/ በዚያን ጊዜ ሕማማት ይጾም የነበረው ጌታ አልዓዛርን ካስነሣበት ከተጽኢኖ ዓርብ ጀምሮ እስከ ትንሣኤ እሑድ ፲ ቀን ስለነበረ ፤ ጾመ ሕርቃል ፯ ቀን እሑድ ሲቀር አሥራ ስድስት ይሆናል ። ይህም ከላይ እንደጠቀስነው በስምንቱ ሱባኤዎች ውስጥ በሚገኙት ከጥሉላት በቀር በማይጾሙት ሰንበታት ሲተካ ፵ ቀን በመቅረቱ በቀጥታ የሚጾመውን ቀን በመቀጠር ጌታ የጾመው ፵ውን ቀን ሁሉ ከቆመ ሳያርፍ ከዘረጋ ሳያጥፍ ፤ ነውና ዕረፍት የሚደረግባቸውን ዕለታት ከአጽዋማቱ ለመለየት ወስነውታል ።

# በቤተ ክርስቲያን ያለው መልክ

፭ኛ ቅዱስ ያሬድ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ታሪክ በመመርመርና በመረዳት የአባቶቻችንን ድንጋጌ በመከተል ጾምነቱን አጽድቆ ከትበላ ዋዜማ ጀምሮ የጌታችንን ሰው መሆንና ለኛ ብሎ መስቀሉን እያወሳ የጾም ድጓ የተባለውን መዝሙር ሲያዘጋጅ ይህንኑ ጾመ ሕርቃልን እንደ ዓቢይ ጾም አድርጎ ከቀዳሚ ይዞ «ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ ወሚመ ኢየእመሩ እግ



www.ethiopianorthodox.org

ዚአ ኩሉ ዘያሐዩ በቃሉ» እያለ ፡ ኢሎድም «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት» እያለ ፤ ቀጥሎም «ሙሴኒ ጾመ በሲና» እያለ ፡ ጾምን በማሞገስ ስለዘመረ ፤ የጾመ ሕርቃል መልክ በቤተ ክርስቲያን ታዋቂ ሆኗል ።

፪ኛ/ ጾመ ሕርቃል በያሬድ እንደ መዘመሩና በአባቶች እንደ ተወሰነ በመመልከት ፤ አባቶች ቀሳውስትና መነኮሳት ከአርባው ቀን ባለመለየት ሥርዓተ ቅዳሴ እንዲደረግበት ዕጣነ ሙገር እንዲቆምበት በማድረጋቸው ፤ እንደዚያው ጌታ እንደ ጾመው እንደ አርባው ቀን በመልኩ ታውቆ አስፈላጊነቱ ጸድቆ በጿሚዎች ልቡና ተጠንቅቆ እየተጾመ የሚኖር በመሆኑ በእእመናን ዘንድ የታወቀ መልክ ተሰጥቶት ይኖራል ።

## ከሕዝብ ልማድ ጋር ያለው ግንኙነት

ይህ ጾም በሕዝብ አነጋገር ሁለት ወር ሁዳዴን መጾም ግድ አለብን እየተባለ ስለሚነገር ፤ የጾሙ ጊዜያትም ለሁለት ወር አራት ቀን ብቻ ስለሚቀረው ፤ ጾሙም ይህን ያህል ቀን መሆኑ ጾመ ሕርቃልና ሕማማት ተጨምረው ስለሆነ ፤ ከሕዝቡ ጋር የተለመደ ግንኙነት እንዳለው በዚህ ለመታወቅ ይቻላል ።

፪ኛ/ በላይኛው ዓምድ እንደተጠቀሰው ክርስቶስ አርባውን ቀን የጾመው በሙሉ ዕረፍት ሳይሻ እንደመሆኑ መጠን ፤ ጾመ ሕርቃልና ሕማማት ሲጨመሩ ከአምሳ ስድስቱ ቀኖች ዕረፍት የሚደረግባቸው አሥራ ስድስቱ ቀኖች ተቀንሰው የሚተርፉት ፵ ቀኖች ያለ ዕረፍት በጸሎትና በስጊድ መጾም ዋና የሕዝቡ ልማድ ስለሆነ ፤ ጾመ ሕርቃልና ጾመ ሕማማት የተቀነሱ እንደ ሆነ ሰንበታቶቹ የዕረፍት ቀኖች ተብለው ከቍጥር ውጪ ሲሆኑ ፤ የአርባው ቀን ቍጥር ስለሚጎድል በሕዝቡ ዘንድ የጾመ ሕርቃል ከዓቢይ ጾም መቈጠር በጾመ ድጓውም ሆነ በምእዛሉ የተለመደ ሆኖ ሲሠራበት መኖሩ የልማድ ግንኙነት እንዳለው ለማረጋገጥ ይቻላል ።

፫ኛ/ ሕርቃል አይሁድንና ፎቃን ስለገደለ ፤ ያልገደሉ ምእመናን መጾማቸውን ልማድ በማድረግ ብዙ ክርስቲያኖች የርጥባን ጾም በማለት አንድ ሰው የንስሐ ጾም ተቀብሎ ለመጾም በደዌ ፤ ወይም በሌላ ምክንያት ሴት ብትሆን በዕንስ ፤ ወይም ባራስነት ምክንያት ለመጾም ሳይችል ፤ (ሳትችል) የቀሩ እንደ ሆነ ፤ ዘመድ ወዳጅ እንዲጾሙላቸው ይደረጋል ። ይህም ከሕዝብ ጋር ያለውን የልማድ ግንኙነት ያስረዳል ።



## ጥቅሙና ጉዳቱ

የጾምን ጠቃሚነት ለሚረዱና ለሚያምኑ ምእመናን ፤ ጌታችን ከቆመ ሳያርፍ ፤ ከዘረጋ ሳያጥፍ ፵ መዓልት ፤ ፵ ሌሊት መጾሙን እያስታወሱ እጸድቅ የማይል አማናዊ ጸድቅ ፤ እከብር የማይል ሉዓላዊ ክቡር ፤ እነግሥ የማይል ዘለዓለማዊ ንጉሥ የሚሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ ሲል መጾሙንና ለኛ መሪ አስተማሪ ለመሆን የጾመ መሆኑን በማሰብ ፤ ለነቀፋና ለትችት ሳይሆን ፤ በፍቅርና በትሕትና በሰጊድና በጸሎት ፤ በዝማሬና በምጽዋት ለሚጾሙ ሰዎች ፤ በፈጣሪያችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋ የሚያሰጥ ስለሆነ ፤ ጥቅሙ በጣም የታወቀ ነው ። ይህንንም ጥቅም ለማግኘት ተስፋ የሚያደርጉ ሰዎች በነዚህ በስምንቱ ሱባኤዎች ከሰንበታቱ በቀር ምሳ ስለማይበሉ የምሳቸውን ሚሳብ አስበው አጠራቅመው ለነዳያን የሚመጸውቱ ናቸው ። ጥቅሙ ይህ ሲሆን ፤ ጉዳቱ የሚከተለው ሆኖ ይገኛል ።

አዲስ አማንያን ከኢአማኒነት ወደ ኢትዮጵያ አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት በሰባክያን ጥረትም ቢሆን ፤ ራሳቸውም የሃይማኖቱን ጠቃሚነት ተመራምረው በመረዳትም ሆነ ፤ የተመለሱ ምእመናን የጾም ብዛት ጠቃሚ መሆኑን ገና ያልተገነዘቡ ሰዎችን እያሠቀቀ የሚያሸሻቸው በመሆኑ ፤ ይህ የጾም መደራረብና መብዛት ብዙ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ መገኘቱ የማይጠረጠር ነው ።

## ሊደረግ የሚገባው መሻሻል

መሻሻል ከተፈለገ ጾም ምግባር እንጂ ፤ ሃይማኖት አለመሆኑን ጠልቀው ለሚረዱ ሰዎች መሻሻል የማያሻው ሃይማኖት ብቻ ስለሆነ ፤ ጾምን እንደ ሃይማኖት ከሚቆጥሩ የዋሆች ሰዎች በቀር ከውጭ ከሌላ ሃይማኖት ፤ ወይም ከኢመኔነት እየመጡ በተዋሕዶ ሃይማኖት የሚገቡት አዲስ አማንያንን እያሠቀቀ ወደኋላ የሚመልሳቸው እንዳይሆን በሊቃውንት ጉባኤ ተመክሮበት ሥርዓተ ጾም ተሻሽሎ ቢደነገግ ጠቃሚ ሳይሆን እንደማይቀርና የጾምን ኃይል በመናፍራት የተዋሕዶ ሃይማኖትን እየሸሹ ወደ ልዩ ልዩ ሃይማኖት የሚያመልጡትን ወጣቶች ለመሰብሰብ እንደሚያስችል እርግጥ ሳይሆን አይቀርም ። ፍትሐ ነገሥት ግን ጾመ ሕርቃል ፎቃ በኢየሩሳሌም ሕርቃል በሮም ነገሡ ሳሉ ፤ ፎቃ በምእመናን ላይ መከራ ስላጸናባቸው ፤ ወደ ሕርቃል ተላልከው ሕርቃል ፎቃን አስገደለው ይላል ።

አለቃ ደስታ ሀብተ ገብርኤል ።



www.ethiopianorthodox.org

ለማስረጃ ያህል የክርስቶስን ስሙነ ሕማማት ስታከብር የሚነበቡ መጻሕፍት ድርሳናትና የተአምራት መጻሕፍት የሚዜሙትም ድርሰቶች ሁሉ በግእዝ ቋንቋ የተሸፈኑ ስለሆኑ ለወጣቱ ትውልድ ተርጉሞ የማስረዳትና የማስተማር ግዴታ አለባት ።

እንዲሁም የአገልግሎቱ ብዛት ከሕዝቡ የኑሮ ትግል ጋር ሲመዛዘን «ያለ ጉታው ደረባው» እንደሚባለው ሆኖ ከመጠን ያለፈ ድካምንና መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ሆኖ ስለተገኘ ብዙውን አገልግሎት ካህናቱ በበኩላቸው ለመፈጸም ፈቃደኞች ቢሆኑም ወጣቱ (አዲሱ) ትውልድ በተለይ ሊፈጽመው የሚገባውን አገልግሎት በተሻለ ዘዴ ማሳጠርና መወሰን ይኖርባታል ። ያለዚያ ግን ከወጣቱ ወገን ብዙ ትውልድ ከቤተ ክርስቲያን እየራቀ እንዳይሔድ ያሠጋል ። ለዚህም ሁሉ አፈጻጸም ሊቃውንትና ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ተስማምተውበት በሰፊው እንዲጠና አስፈላጊ መሆኑን ልዘነጋው አይገባም ።

መክብብ አጥናው ።



# ጸሎተ ሐሙስ

እንደ ሥነ ፍጥረት አቈጣጠር ሐሙስ ከሰባቱ ዕለታት በአምስተኛው ተራ ቍጥር የሚገኝ አንድ ዕለት ነው ። ይህ ቀን በአንድ ዓመት ውስጥ ሃምሳ ሁለት ጊዜ በመገኘት የተወሰነውን ዓመታዊ ቍጥር ያሟላል ።

ኑሮ በዕለታት እየተመጠነ መተንተን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የሰው ልጅ አንድ ከፍተኛ ተግባር የፈጸመበትን ቀን ልዩ ዘርፍና ቅጽል ሰጥቶ መጥራቱ የተለመደ ነው ።

በዚህ ዓይነት-ይህ ሐሙስ በመባል የታወቀው ዕለትም በብሔራዊ ባህላችንና ቋንቋችን ፤ ከሕዝብም በቤተ ክርስቲያንም በኩል የተለያየ የግብር ስም ተሰጥቶት ፤ በአንድ በኩል «ጸሎተ ሐሙስ » የሚል ስያሜን ሲያገኝ በሌላ በኩል ደግሞ «ዕብድ ሐሙስ ፤ አዳም ሐሙስ» እየተባለ ይጠራል ።

አሁን የጸሎተ ሐሙስን ብሂል ፤ ከመዘርዘራችን በፊት አስቀድመን ይህ ዕለት ለምን «ዕብድ ሐሙስና የዓዳም ሐሙስ» እንደተባለ ምክንያቱን መግለጽ ሳያስፈልግ አይቀርም ይሆናል ።

በሀገራችን «ዘመነ መርዓዊ » እየተባለ የሚጠራ አንድ የጋብቻ ክፍለ ጊዜ አለ ፤ ይኸውም ከታኅሣሥ ጾም መፍቻ ቀጥሎ እስከ ዓቢይ ጾም ቅበላ ድረስ ያለው ጊዜ ነው ።

የዓቢይ ጾም ስኞ እየተቃረበ ሲሔድ በዚያ ግድም ያሉ ዕለታት ለጋብቻ ተፈልገው አይገኙም ። በጣም የተወደዱ ናቸው ። በተለይም ሐሙስ በረቡዕና በዓርብ የተከበበ ዕለት ስለሆነ በዚህ ቀን እንደ ሀገራችን ባህልና ሥርዓት የሠርግ ሆታና ዕልልታ ፤ ዘፈንና ጭብጨባ እንዲሁም በጠቅላላ የደስታ ድምፅ የማይሰማበት ሠፈር አይገኝም ፤ በዚህ ምክንያት ይህ ዕለት በሕዝቡ ዘንድ «ዕብድ ሐሙስ» ተብሎ ተሰይሟል ።

ይህ ከዓቢይ ጾም በፊት ለሚውለው ዕለተ ሐሙስ የተሰጠ ስያሜ ሲሆን ከዓቢይ ጾም በኋላ ወይም ከትንሣኤ ቀጥሎ የሚገኘው ሐሙስ ደግሞ «ዓዳም ሐሙስ» ይባላል ። ይህም በእንጨት ፍሬ ምክንያት ወደ ዓለም የገባውን ኃጢአት ለማስወገድ «በሐሙስ ዕለት ወበ መንፈቀ ለዕለት ------» ማለት በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ እወለዳለሁ ሲል እግዚአብሔር ለዓዳም የሰጠው የድኅነት ተስፋ በቀጠሮው ቀን መፈጸሙን የሚያስታውስ አንድ የመታሰቢያ ዕለት ነው ። « የቀጠሮው ቀን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር አንዱን ልጁን ወደ ዓለም ላከ ። ከሴትም ተወለደ» ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ የጠቀሰውም ይህን መሠረት በማድረግ ነው ። ገላ ፬-፭ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሁኖም አሁን ለማወቅ የፈለግነው ስለ ጸሎተ ሐሙስ በመሆኑ ሌላውን ሐተታ ከዚሁ ላይ አሳርፈን ወደዋናው ዓላማችን እንመለስና ፤ ጸሎተ ሐሙስ የሚለው ቃል በትክክል ሲነበብ «የጸሎት ሐሙስ» ማለት ነው ፤ የጸሎት ሐሙስ ማለትም በግልጽ ሲተረጐም «የጸሎት ቀን» ማለት ነው ።

ጸሎተ ሐሙስ የሚገኘው በሆሣዕናና በትንሣኤ እሑድ መካከል ባለው ሳምንት ውስጥ ሲሆን መታሰቢያነቱም በክርስትና ዓለም ላይ ከፍተኛውን ሥፍራ ፤ ይዞ ይገኛል ።

## የ ት መ ጣ ው

ይህ ዕለት ጸሎተ ሐሙስ ወይም የጸሎት ሐሙስ የሚለውን ስያሜ ያገኘው ከክርስትና ወዲህ ነው ። በዚህ ዕለት በቤተ ክርስቲያን የሚታየውና የሚሰማው ሁሉ ጸሎትና ሥነ ሥርዓት ፤ ክርስቶስ ዓርብ ሊሰቀል ፤ ሐሙስ ማታ ያደረገውንና ያቋቋመውን ሐዲስ ሥርዓት በግልጽ የሚያሳይ ታሪካዊ ሁናቴ ነው ።

ክርስቶስ ለታላላቅ ሰዎች ትሕትናን ያስተምር ዘንድ በዚህ ዕለት ራሱን ዝቅ አድርጎ የተማሪዎቹን እግር አጠበ ።

የሰው ልጆች ን ድካምና ወጭ ለመቀነስ ሲልም ለኃጢአት ማስተሥሪያ ይቃጠል የነበረውን የላምና የበግ መሥዋዕት አሻሽሎ በቀላሉ የሚገኘውን የስንዴና የወይን መሥዋዕት በመተካት ታላቅ ለውጥ አደረገ ። ይህ በበግና በፍየል ፋንታ የተተካው የስንዴና የወይን መሥዋዕትም ስለዓለም ድኅነት በመስቀል ላይ የተፈተተው የራሱ አማናዊ ሥጋና ደም መሆኑን አረጋገጠ ። ጸሎትም ጸለየ መዝሙርም ዘመረ ፤ ስለዚህ ጸሎተ ሐሙስ ተብሏል ከዚህ በኋላ መሥዋዕትነቱ በዚሁ ዓይነት ወደፊት እንዲቀጥል ፈቃድና ሥልጣን ሰጠ ።

ለዓለም ጸሎትና ስግደትን ያስተምር ዘንድም በጌቴሴማኒ (የተክል ቦታ) ራሱን ወደ ምድር ዝቅ አድርጎ ሰግዶ ጸለየ ። ጸሎትና ስግደት ፍጡር ለፈጣሪው ሊፈጽመው የሚገባ የተገዥነት ምልክት መሆኑን ለማወቅ ከዚህ የበለጠ ማስረጃ የለም ። ይኸንም ለደቀመዛሙርቱ ሲያስተምር በሥራ ገልጦታል። ከጸሎቱም በኋላ ለተማሪዎቹ «ሥጋ ደካማ ነው መንፈስ ግን ብርቱ ነውናወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ» ሲል ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጠ ።

ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ቀን ጸሎተ ሐሙስ ተብሎ ይጠራ ጀመር ።

## በቤተ ክርስቲያን ያለው ይዞታ

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ቃል ተቀባይና ፈጻሚ ወይም አስፈጻሚ እንደ መሆኗ መጠን ክርስቶስ አርአያውን ለማሳየት ጸሎትና ስግደት ያደረገበትን እንዲሁ በጠቅላላም መሥዋዕተ ኦሪትን ሽሮ መሥዋዕተ ወንጌልን በመተካት



ታላቅ ለውጥ ያደረገበትን ያን ዕለት «ጸሎተ ሐሙስ» ብላ ሰይማ መታሰቢያውን በጸሎት ታከብራለች ፤ ክርስቶስ ዝቅ ብሎ የሐዋርያቱን እግር በማጠብ ያሳየውን ምግባረ ትሕትና በግብር በመግለጽ አገልግሎቱን ለዓለም ትመሰክራለች ።

ሁላችንም በዚህ ዕለት ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሔድ ፤ ጳጳሱ የቄሱን ቄሱ የጳጳሱን እግር በአጭር ታጥቆ በወይን ወኃ ሲያጥብ ለማየት እንችላለን ፤ ይህ ምንጊዜም የጸሎት ሐሙስ ዕለት በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸም የመታሰቢያ ሥነ ሥርዓት ነው ፤ ከዚህም በቀር ሁል ጊዜ በሰሙነ ሕማማት የቅዱስ ቍርባን ስጦታ በዚህ ዕለት ዝግጅቱ ቀጥሎ ለተቀባዮቹ ይቀርባል ።

አሁን ሁላችንም የምንቀበለው ቅዱስ ቍርባን ከስንዴና ከወይን ተዘጋጅቶ በጸሎተ ቅዳሴ የተለወጠ የክርስቶስ አማናዊ ሥጋና ደም መሆኑን ያለ ጥርጥር እናምናለን ፤ ይህ ዓይነት ምሥጢራዊ ለውጥ በቤተ ክርስቲያን ፀንቶ የቀረውም ክርስቶስ ዓርብ ሊሰቀል ፤ ሐሙስ ወደ ማታ ተማሪዎቹን ሰብስቦ ይህ ሥጋዬ ነው ። ይህም ደሜ ነውና እንኩ ብሉ ጠጡ ብሎ ኅብስትና ወይን ከሰጣቸው ወዲህ ነው ። ስለዚህ ጸሎተ ሐሙስ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው ይዞታ የሞቀና የደመቀ ነው ።

## በሕዝብ ላይ ያስከተለው ልማድ

አንድ ጊዜ የተደረገ ነገር ድርጊቱ ሳያቋርጥ ከቀጠለ ከጊዜ በኋላ ልማድ እየሆነ ይሔዳል ።

ልማድ የሚባለውም ሕዝቡ እንዴት እንደተጀመረና ለምን እንደሚደረግ ትርጉሙን ሳያውቅ በየጊዜው ሲፈጽመው የሚታየው ከባህል ጋር የተወሳሰበ ተግባር ነው ።

በዚህ ዓይነት ይህ ጸሎተ ሐሙስ የተባለውም ዕለት የጉልባን የንፍሮ መቀቀልንና ዳቦ የመጋገርን ልማድ በሕዝቡ ላይ አስከትሏል ።

ምንም እንኳን በአንዳንድ አገር ፤ ዳቦ የትንሣኤ እንጂ የጸሎት ሐሙስ ዕለት መጋገር ብዙ የተለመደ ባይሆንም አብዛኛውን ሕዝብ የጸሎት ሐሙስ ዕለት ንፍሮ ይቀቅላል ዳቦ ይጋግራል ።

ሁኖም ሕዝቡ ይህ ልማድ ከምን ተነስቶ ከዚህ እንደደረሰ ምንጩንካውቀው ልማድና ባህሉ የሚነቀፍ አይደለም ። ሟርትና አምልኮ ያልተቀላቀለበት ንጹሕ ልማድ ነው ።

የልማዱም አመጣጥ እንደሚከተለው ነው ፤ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ያረገው የሥነ ሥርዓት ለውጥ በቤተ ክርስቲያን በኩል በላምና በበግ ፈንታ



www.ethiopianorthodox.org

የስንዴና የወይን መሥዋዕትን ተክቶ ሲሔድ ፤ በሕዝቡ በኩል ደግሞ የዳቦ መጋገርንና የንፍሮ መቀቀልን ልምድ ስለአስከተለ ይኸው በዚህ ዓይነት የዕለቱ መታሰቢያ ሲደረግ ይታያል ።

ትርጕሙና የትመጣው ይህ መሆኑ ከታወቀ ልማዱ ወደ ፊት ቢቀጥል በሕዝቡ ላይ ምንም የሚያስከትለው ጉዳት የለም ።

## ማጠቃለያ

ስለ ጸሎተ ሐሙስ ከብዙው በጥቂቱ ልናውቀው የሚገባን ይህ ነው ፤ ይኸውም ከጸሎተ ሐሙስ ሥርዓት ብዙው በቅዱስ ወንጌል ያለና የተጻፈ ቃል በመሆኑ ለብዙዎቻችን እንግዳ ሊሆን አይችልም፤ሁኖም ያኑ የምናውቀውንም ደህና አድርገን ማወቅ ስለሚኖርብን ይህን አጭር ትምህርታዊ መግለጫ ለም እመናኑ ማበርከት አስፈላጊ ሆነ ።

ጸሎተ ሐሙስ ፤ በቤተ ክርስቲያንም በሕዝቡም ዘንድ አንድ ዓይነት ዓላማ ያለው መሆኑ ቢታወቅም የመታሰቢያው ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለያየ መሔድ ጀምሮአል ፤ ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ይህን ዕለት የምታውለው በጸሎትና በስግደት ፤ የክርስቶስን ውለታ በመነጋገር ሲሆን ሕዝቡ ግን የዚህን ዕለት መድረስ የሚጠባበቀው ለዳቦ ጋገራና ለንፍሮ ቅቀላ ሁኗል ። የሚያሳልፈውም ዳቦ በመቁረስ ንፍሮ በመቅመስ ነው ። እውነት ነው ፤ ሕዝቡ የጸሎተ ሐሙስን ዝግጅት እንደ ልደታ ንፍሮ ዓላማውን ሳይለ ውጥ ፤ የቆሴና የባዕድ አምልኮ መንፈስ ሳይቀላቀልበት ፤ ዳቦውንም የጉልባን ንፍሮውንም ከሚርት ንጹሕ በሆነ ልማድ ሲፈጽም በመገኘቱ ሊመሰገን ይገባዋል ። ሁኖም የቀረውና የጐደለው ነገር ስለአለ ምስጋናው ወደ ነቀፋ ሳይለወጥ ጉድለቱን አውቆ ማስተካከል የክርስትና ዓላማ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል ።

ጉድለቱም ክርስቲያናዊው ሕዝብ በዚህ ዕለት አልፎ አልፎ እንደሚታየው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔዶ ከካህናቱ ጋር የጸሎቱ ሥነ ሥርዓት ተካፋይ ሳይሆን ወደዳቦውና ወደ ንፍሮው በመሠማራቱ ነው ።

የምግብ መቅድሙና ማሳረጊያው ጸሎት ስለሆነ ሁል ጊዜ ከምግብ በፊት እንጸልይ ፤ በተለይም ይህ ዕለት የጸሎት ቀን በመሆኑ ሁላችንም ለጸሎትና ለስ ግደት ወደ ቤተ ክርስቲያን መገሥገሥን እንርሳ ፤ መብላችንም ምድራዊ ዳቦ ብቻ ሁኖ እንዳይቀር በዚህ ዕለት ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል ቸል እንበል ።

ቀኝ ጌታ ተሾመ ዘርይሁን ።



# ቀዳም ሥዑር

ይህ ዓይነት ስያሜና አጠራር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባህልና ሥር ዓት መሠረት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የቆየ ነው ። « ቀዳም ሥዑር » ማለት የተ ሻረ ቅዳሜ ማለት እንደሆነ ይነገራል ። በዚህም ዓይነት ለምሳሌ ፤ በአገር ቤት ጥዋት ቄጠማ እስኪዞር ድረስ እህል ይፈጫል ። ውኃ ይቀዳል የመሳሰሉ ትም ሁሉ ሥራዎች ይሠራሉ ። ይህም በሰንበተ አይሁድ ቀዳሚት ለመጀ መሪያ ጊዜ የተሻረችበት ዕለት ነው የሚል ልማዳዊ አነጋገር አለ ። ነገር ግን ይህ ስያሜ ሕዝቡ ለሥራ ስለጓጓ የፈጠረው እንጂ ፤ ከቤተ ክርስቲያን የተ ገኘ አይመስልም ። ቀዳም ሥዑር በሌላ በኩል ደግሞ ለምለም ቅዳሜ ማለት እንደሆነ የሚአትቱ አሉ ። ሆኖም የቃሉ ፍች ምንም ያህል ጠቃሚ ስለአል ሆነ ፤ ይህን ከዚህ ላይ አልበን ፤ በዚህ ዕለት የሚፈጸሙትን ሌሎችን ልማ ዶች ለመግለጽ እንሞክራለን ።

የቀዳም ሥዑር ዕለት ጥዋት ካህናት በቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ጸሎትና ሥርዓት ከፈጸሙ በኋላ ፤ በሱቱ የተጠቀለለ ለምለም ቄጠማ ይዘው በየመንደሩ እየዞሩ « ጌታ ተመረመረ ዲያብሎስ ታሠረ » እያሉ የምሥራች ምልክት የሆነውን ቄጠማ ለምእመናኑ ይሰጣሉ ። እንዲሁም በጸናጽል በከ በሮ «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ» እያሉ እየዞሩ በማሸብሸብ የምሥራቹን ይገል ጻሉ ። ካህናቱ በአንዳንድ ጠቅላይ ግዛቶች ገብረ ሰላም ከሚያበላው ሰው ቤት የምሥራቹን ቄጠማ ከቤት ውስጥ ገብተው ሲሰጡ ፤ ከሌላው ደግሞ ከውጭ እንደቆሙ ይሰጣሉ ። ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ቄጠማውን በሚሰጡበት ወቅት ሴቶች ልቃቂት (ልቅ) ይሰጣሉ ። ይህም ልቃቂት ተሰብስቦ ለጧፍ ይሆናል ። ይህ በገጠር በብዙዎቹ ክፍለ ሀገሮች ይደረጋል ። ይህ የቀዳም ሥዑር ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙት ሲሆን ፤ ከሕዝቡ ልማድ ጋር የተያያዙ ልማ ዶችም በዚህ ዕለት ይፈጸማሉ ። በብዙዎቹ ጠቅላይ ግዛቶች በዚህ ዕለት ማታ አክፋዮች ቂጣ ጋግረው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ በቄስ አስባርከው ይበ ላሉ ። ይህ የአክፋይ ምግብ (ዳቦ) በሸዋ ተስፋ የሚል ስያሜ ሲኖረው በጎ ጃም ደግሞ በአንዳንድ ቦታዎች ምስለ ኩኪ ይባላል ። አክፋይ ያልሆነ ሰው



www.ethiopianorthodox.org

ይህን ዳቦ አይበላም ። ይህ ምስለ ኲክም ሆነ ተስፋ በሚል ስያሜ የሚጠራው የአክፋይ ምግብ የሚደገፍ ነው ። ምክንያቱም በአንዳንድ ክፍለ ሀገሮች አክፍሎት ከሐሙስ ማታ ጀምሮ እስከ እሑድ ሌሊት ድረስ ማለት ለ፶፯ ሰዓቶች ያህል እህልና ውኃ ሳይቀምሱ የሚያከፍሉ ሰዎች ስለአሉና ፤ በኋላ በፋሲካው ቅባት ዘለቅ ተከታታይ ድግስ ምክንያት ድርቀት የሰነበተበትን ሆድ ከመጠን ያለፈ ቅባት ሲጐበኘው በአጣዳፊ የተቅማጥ በሽታ ከሞት የሚደርሱ ብዙዎች ስለሆኑ ፤ አክፋዮች ከዚህ ሁሉ የድካም አደጋ ለመዳን ይችሉ ዘንድ ይህች ተስፋ ፤ ወይንም ምስለ ኲክ የተባለች አነስተኛ ዳቦ ስለምትረረዳ ፤ በሁሉም ዘንድ ይህ ዓይነት ልምድ ቢኖር መልካም ስለሚሆን ነው ። አንድ ሰው ፶፯ ሰዓቶች ያህል እህል ሳይበላ እንዲቆይ ማዘዝ ድካምን ስለሚያስከትልና በሰው ላይ ጉዳትን ስለሚያመጣ አሁን ያለው የአክፍሎት ይዞታ ሊሻሻል ይገባዋል ። ምንም እንኳን የጌታችን የመድኃኒታችንን ሞትና ፀዋትወ መከራ በማሰብ የትንሣኤውን የምሥራች እስኪሰሙ ድረስ ከማንኛውም ምድራዊ ደስታና ከእህል ከውኃ ሳይቀር ተከልክለው ምእመናኑ በስግደትና በጸሎት መቆየታቸው የሚአስመሰግን ታላቅ የክርስቲያንነት ምልክት ቢሆንም ፤ በባዶ ሆድ በሚደረገው ከፍተኛ ስግደትና ጸሎት ፣ ምክንያት ብዙ ሰዎች ከአደጋ ላይ ስለሚወድቁ ፤ አክፍሎት ጨርሶ እንኳን ባይቀር ሊሻሻል ይገባዋል ። በእኔ አስተያየት አክፍሎት ከቀዳም ሥዑር ማታ እራት ብቻ መከልከል እንኳን ቢሆን በቂ ይመስለኛል ። ይሁን እንጂ ፤ የአክፍሎት ድካም ሊሰማቸው የሚችለው ሽማግሌውን ክፍል እንጂ ዘመናዊውን ወጣት የሚ አሳስብ አይደለም ። ወጣቱ ትውልድ እንደሚታየው እንኳንስ አክፍሎትና ተራውንም ጾም እንኳን በፈቃዱ ሰርዞት ስለሚታይ ነው ።

የለምለም ቄጠማው እያዞሩ መስጠት ግን የታላቅ ምሥራችነት ምልክት ስለሆነ ፤ የሚደገፍ ነው ። የዚህን መልካም ልምድ የትመጣ አባቶች ሲናገሩ ማየ አይህ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ከዘነመ በኋላ ፤ ኖኅ መርከቡን ከፍቶ ርግብን የውኃውን መጉደል አይተሽ ነይ ሲል ላካት ። እርሷም በትእዛዙ መሠረት ሔዳ የውኃውን መጉደል ከተመለከተች በኋላ ፤ ለምለም የወይራ ቅጠልም ይላሉ ። ወይንም ቄጠማ በአፏ ይዛ ወደኖኅ ተመለሰችና የምሥራች « ሐፀ ማየ አይኅ ፤ ነትገ ማየ አይኅ» የዘነመው የፍልውኃ ዝናም ፈጽሞ ጉድሏል ፤ ደርቋል ስትል ነገረችው ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ በክርስቶስ ስቅለትና ሞት ከአዳም ጀምሮ የተከማቸው የኃጢአት ባሕር ውቅያኖስ ደረቀ ፤ ነጠፈ ስትል ይህን የምሥራች ለምለም ቄጠማ በዚያች ርግብ አምሳል ለምእመናኗ ታድላለች ይላሉ ።

ይህ ሥርዓት መቀጠል የሚገባው ቅዱስ ሥርዓትና ባህል ነው ። ይህ ቅዱስ እምነት ፤ ልማድ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሙሉ በኃጢአት ምክንያት ተዘግቶ የነበረው የጽድቅ በር መከፈቱን ያበሥራል ፤ ያውጃል ፤ ስለዚህ መቀጠል እንጂ መቅረት የለበትም ።

አእምሮ ወንድምአገኘሁ ፤





www.ethiopianorthodox.org

# የልደታ ንፍሮ

የቃሉ ትርጉም ግንቦት ፱ነኛ ወር ማለት ሲሆን የቃሉ ፍቺ ወይም ትርጉም በግእዙ ሰዋስው (ግንብዋት) ፊቀን ወይም ጋር ማለት ነው ። በአማርኛ ግንቦት ወይም ገንቦዎች ማለት ይመስላል ፤ መቼም ገንቦ ፤ እንስራ ወይም ፊቀን ቢባልም ከሸክላ ሥዕሎች ውስጥ አልወጣም ፤ ሊቃውንቱ እንደሚሉት ግንቦት የሚባለው ወር በሸክላ ዓይነቶች የተጠራበት ምክንያት የገንቦ ዓይነት ሸክላዎች ውስጣቸው ክብ የሆነ አንገተ ጠባቦች አየር በብዛት የማይገባቸው ስለሆኑ የግንቦት ወርም በዚሁ ምሳሌ ሙቀት የሚበዛበትና ንጹሕ አየር የሌለው ድፍን በመሆኑ ነው እያሉ ይተረኩሉ ።

በዚህም ምክንያት የግንቦት ወር በጣም ሙቀት የበዛበት በመሆኑ አንዳንድ አገሮች በሙቀት ጊዜ ተቃቅፎ መተኛት ጤና አይሰጥም አስፈላጊ አይደለም በማለት ጋብቻን ይከለክላሉ ።

## የግንቦት ልደታ ንፍሮ

በዋግ አውራጃ በኩረም ከተማ የእህል ዓይነቶች ሁሉ ተሰብስበው ከመንደሩ ወይም ከከተማው አካባቢ ትልቅ ዳስ ይሠራና ከዚያ ውስጥ ሴቶች ሁሉ ተሰብስበው ከጧቱ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ይቀቅላሉ ፤ በስለትና በመዋጮ የተሰበሰበው ገንዘብ እንደ መጠኑ ብዙ በግና ዶሮ ይገዛና ይታረዳል ፤ ሰባት ሰዓት ሲሆን ወንዶች ሁሉ ከየሥራቸው ይሰበሰባሉ ፤ ከዚያ በኋላ አንድ ትልቅ የሆነ የመንደር ሽማግሌ ይነሣና ሁለቱን ወጣቶች የሆኑ ወንዶች ልጆች ብትር አንስቶ አንገታቸው ላይ አድርጎ እንደሚያርስ በሬ አጉንብሰው እንዲሔዱ አድርጎ በጅራፍ እየነዳ ንፍሮውን እንደ ዘር ይበትነዋል ፤ በኋላ ልጆቹ ተለቀው ለበዓሉ የተዘጋጀው ድግስ ቀርቦ ይበላና ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ስለ ችግራቸው ይሳላሉ ፤ ሽማግሌዎችም ይመርቋቸዋል ፤ በዓሉም እስከ ሦስት ቀን ድረስ ይፈጸማል ።

በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ባህሉ የተለያየ ነው ፤ የግንቦት ልደታ ዕለት በየአንዳንዱ ቦታ ቆሎ ይቆላል እንጂ ንፍሮ አይቀቅልም ፤ ደግሞ በብዙ ቦታ በግ ወይም ፍየል ይታረዳል ። ነገር ግን ከድግሱ የተረፈው በየትም አገር ቢሆን ወደቤት አይመለስም ። በሸዋ ጋብቻም የለም ።



# ትግሬ በሽሬ አውራጃ

የግንቦት ልደታ ከእህል ዓይነቶች ሁሉ አንድም ሳይቀር እንዲያውም የሚያስገርመው ነገር ኑግ ፤ ጤፍ ፤ ዳጉሳ ሳይቀር አብሮ ይቀቀልና አሥር ሰዓት ገደማ ሲሆን አንድ ትልቅ ሰው ተነሥቶ በሁለት ልጆች ጫንቃ ላይ በትሩን አጋድሞ እንደ በሬ አስጎንብሶ ፤ በጅራፍ ልጆቹን እየነዳ ፤ ንፍሮውን እንደ ዘር ይዘራዋል ፤ ከዚህ በኋላ ምህላ ጸሎት እግዚአታ ይደረግና ንፍሮው ይበላል ፤ ሁሉም በየዓይነቱ የተገኘው ሁሉ ይበላል ፤ ይጠጣል ። ከጥቂት ቀን በኋላ የተዘራው የንፍሮ ዓይነት ሁሉ ተጭሮ ይታይና እንደ ብቅል አጉንቁሎ (አብቅሎ) የተገኘው የእህል ዓይነት ይታይና በቅሎ የተገኘው ክፍል ትንቢት ይነገርለታል ዘንድሮ ይህ ዓይነት ይሆናልና እንድትዘሩ እየተባለ ይነገራል ። ጋብቻ አለ ።

ሁለተኛ ደግሞ በአክሱም ፤ በአድዋ ፤ በተንቤን አውራጃ እንዲህ ይደረጋል ፤ ምንጊዜም ቢሆን የንፍሮው ሰዓት በሁሉም ቦታ ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ፤ በነዚህ አውራጃዎች ንፍሮው ለዚሁ ከሚያገለግሉ ጥርጣጣሬዎች ተሰብስቦ ይቀቀልና ከበሰለ በኋላ ከመቀመሱ በፊት ጥቂቶች ባልቴቶች ይመረጡና ከንፍሮውና ከሌላውም ዓይነት ሁሉ በጥቂቱ ይዘው ወደ ከተማው ዳር ወጣ ብለው ጥለው ፊታቸውን ወደጣሉበት ቦታ ሳይመልሱ በቀጥታ ወደንፍሮአቸው ከተመለሱ በኋላ ሁሉም ይቀመሳል ይበላል ፤ ዘፈንም አለ፤ምርቃን ሁሉ ያጣ እንዲያገኝ መካን እንዲወልድ ይመረቃል ፤ ስለትም የሚሳል አለ ፤ ምርቃቱም ማርያም ትስጥህ የሚል ነው ፤ ከዚህ በኋላ ጸሎተ ምህላ ተደርጎ ይለያያሉ ። በነዚህ አውራጃዎች በዚሁ አንፃር የገና በዓል በልደት ደግሞ ማሽላ ቆሎ ይቆሉና ስለ ጌታችን መወለድ የፈካውን የማሽላ ቆሎ በአፋቸው ውስጥ ይዘው እየቆረጠሙ ዳኑ ፤ ዳኑ ፤ እያሉ በቃለ አጋኖ ይዘምራሉ ። ጋብቻ ግን አለ ።

በጐንደር ግን የግንቦት ልደታ ቀን ንፍሮ መቀቀልና እንዲሁም ቂጣ በኑግ እየታሸ ይቀመሳል፤ በአንዳንድ ቦታ በግ ወይም ፍየል የሚያርዱ ይገኛሉ ፤ ደግሞ ለሚመጣው ዓመት ይህን አደርጋለሁ በማለት ይሳላሉ ፤ ይህም ስለት ፍጻሜ እንዲያገኝ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች ይመርቃሉ ፤ በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ይህንኑ የመሰለ ሥርዓት ነው የሚደረገው ጋብቻ ግን አለ ።

በወሎ(በደሴ)ከተማ ይህንኑ ከዚህ በላይ በጎንደር እንደሚደረገው ዓይነት ሆኖ ሥርዓቱ የግንቦት ልደታ ብቻ ሳይሆን ሁል ጊዜ በየወሩ የልደታ ቀን ንፍሮ ይቀቀላል።

በከንባታ አውራጃ ሆሣእና ከተማ የተቀቀለው ንፍሮ ይዘራል ፤ ያልበቀለ እንደሆን ዘንድሮ ረኃብ ይሆናል እየተባለ ትንቢት ይነገርለታል ።



www.ethiopianorthodox.org

እኔ ደግሞ ሊቃውንት እንደሰማሁት ሰሌኒ ንግሥት ልጅዋ ቈስጠንጢኖስ ንግሥ የሮማ ቄሣር በሆነ ጊዜ እናቱን ከአጠገቡ አምጥቶ ፤ አስቀምጦ ክብርና ሥልጣንም እንዲኖራት ስለ አደረገ ። እርሷም እንደ ልጅዋ የክርስቲያንን ሃይማኖት ትወድ ስለነበረ በሮማ ፤ በቍስጥንጥንያ ፤ በኢየሩሳሌም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሠራች። ወደ ኢየሩሳሌምም እየተመላለሰች ጌታችን የተወለደበት ቤተ ልሔምን ፤ ያደገበት ናዝሬትን ፤ የተሰቀለበት ቀራንዮን ፤ የተቀበረበት ጎልጎታን ስትጎበኝ የጌታችንን መስቀል አስፈልጋ ከተቀበረበት ቦታ በተአምራት ስለአወጣች ፤ በደስታ ተመልታ የቅድስና ሥራዋን አዘወተረች፤ በዚህም ጊዜ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ዜናና የሕይወት ታሪኳን ፤ የቅድስናዋን ፤ የንጽሕናዋን ታሪክ በደንብ ከአጠናች በኋላ እንደ ሀገሩ ባህልና ደንብ አይሁድ የልደት በዓላቸውን ማክበር የሚወዱ ስለሆነ ይህን አይታና ተመልክታ እመቤታችን ድንግል ማርያም በተወለደችበት ቀን የልደት በዓልዋ እንዲከበር አደረገች ።

፩/ የበዓሉም አከባበር ዓይነት እንደ ሀገሩ ልማድ እስራኤላውያን በሚያከብሩት ዓይነት ከግብጽ ባርነት የወጡበትን የፋሲካን በዓል በግ በማረድና የበጉን ደም በማንባራቸው ላይ እየቀቡ እንዴት እንዳዳናቸውና ከግብፅ እንደ ወጡ ዘጸአት ፲፪ ፤ ፩-፶፩ ። በዓመቱ መጀመሪያ ከ፲፬ ቀን ጀምሮ እስከ ፳ኛው ቀን ድረስ የቂጣ በዓል ይከበራል ፤ በእነዚህ ቀኖች ውስጥ አይሁድ ሁሉ እርሾ ያልተጨመረበት ያልቦካ እንጀራ ይበላሉ ። ዘጸአት ፲፪ ፤ ፲፬-፳ ዘዳግም ፲፯ ፤ ፫ ።

፪ኛ/ አይሁድ (ሰዋን) የሚሉት የዓመቱ ሦስተኛ ወር ይህም ወር ግንቦትና ሰኔ በተባሉት በኢትዮጵያ ወራት ውስጥ ነው ፤ እርሱም የመከር ወር ገብ ስም ፤ ስንዴም ወደ ጎተራ የሚከተትበት የክታች ወር ነው ፤ ዘይሌዋውያን ፳፫ ፱/፲፬ ) ። አይሁድ ከሚያዝያ ጀምረው እስከ ሰኔ ድረስ የቂጣ በዓል ፤ የመከር በዓል እያሉ የሚያከብሩዋቸውን በዓላት ምክንያት በማድረግ ፤ እሌኒ ንግሥትም የማርያምን የልደት በዓል በዚሁ አንፃር እንዲከበር አደረገች ይባላል ። ይህም በዓል እያደረ በማጋነን ማርያማዊ አምልኮ ተብሎ ተሰይሞ በምሥራቅና በምዕራብ ቤተ ክርስቲያን መካከል የተለመደ ሆኖ ይኖር ነበር ይባላል ።

ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ዘመን ግን በ፳፻፳፭ ዓመተ ምሕረት ውስጥ ዓፄ ካሌብ ወደ ሀገረ ናግራን (ዓረብ አገር) ዘምተው በተመለሱ ጊዜ ነው ይባላል ። ይህም በሀገረ ናግራን የሚኖሩ ክርስቲያኖች ይህን ከኢየሩሳሌም ተቀብለው ኖሮ ከእነርሱ ደግሞ ይህን መንፈሳዊ በዓል የአፄ ካሌብ ሠራዊት ተቀብሎ ወደሀገሩ ኢትዮጵያ ይዞ ስለመጣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሀገራችን የተለመደ መንፈሳዊ በዓል ሆኖ ይኖራል ።



ለምሳሌ በሀገራችን በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ስንኳ ይህን ልማድ በማድረግ አንድ ሴት ልጅ የወለደች እንደሆነ ፤ መንደረኛው ሁሉ ጐረቤት የሆነው ተሰብስቦ ከአራሲቱ ሴት ቤት ሔዶ ንፍሮ ቀቅሎ ይበላል ።

እኔም በራሴ አስተያየት የሆነ እንደሆነ ከዚህ በላይ በእሥራኤል ሥርዓት ውስጥ እንደጠቀስኩት ሁሉ ፤ የኢትዮጵያ ሕግና ባህል ፤ ሥርዓትና ልማድ ሁሉ ከአይሁድ ጋር በሕግም ፤ በትውልድም ፤ በአምልኮትም የተሣሠረ በመሆኑ ፤ በግንቦት ወር ውስጥ ስለ ልደታ በዓል የሚደረገው ፤ ሥነ ሥርዓትን የተመረኮዘ መንፈሳዊ በዓል ነው እላለሁ እንጂ ፤ ባዕዳዊ አምልኮ ነው አልልም ።

ነገር ግን በአንዳንድ ቦታና በአዲስ አበባ አካባቢ ያለው ሕዝብ ባዕዳዊ አምልኮትን እንዳይጨምርበት ቤተ ክርስቲያንና ሕዝብ ተባብረው ማረም አለባቸው ።

## የግንቦት ጋብቻ

በብዙ ጠቅላይ ግዛቶች የግንቦት ወር እንደሌላው ወር እንጂ ምንም ልዩነት የሌለው በመሆኑ ጋብቻቸውን ይፈጽሙበታል ።

በአንዳንድ ጠ/ ግዛቶች ግን ግንቦት እህሉ የሚያዕዕበት ፤ ድርቅ የሚፀናበት ሥራ ፤ (እርሻ ቁፋሮ) የሚበዛበት ጊዜ በመሆኑ ፤ ለሠርግ ቸል ይሉታል ። አንዳንድ ጠቅላይ ግዛቶች ግን ወደአምልኮት ወስደው ጋብቻን ፈጽመው ይከለክላሉ ። ትርጉም ግን ሊሰጡ አይችሉም ።

አንዳንዶች እንደሚያስረዱት ደረቅ አየር ያለበት ፤ ቁስል የሚጸናበት ጊዜ በመሆኑ፤ለአዲስ ተጋቢዎች በተለይ ለሴቷ ወገን አሥጊ ነው በማለት ይከለክላሉ ።

አንዳንድ ሀገሮች ሀብታቸው እንደፈቀደ የዕረፍት ጊዜ ባገኙበት ጊዜ ሠርግ ያደርጋሉ እንጂ ፤ የወራት ፤ የዘመናት መሰናክልነት አያጋጥማቸውም የግሪክ ሕዝብ ብቻ በግንቦት ወር ሠርግ አያደርግም ። ምክንያቱን ሲጠይቋቸው ቍስጥንጥንያ ከተማቸው በቱርክ የተወረረበት ወር በመሆኑ ፤ የኀዘን ወር ብለው ሰይመውታል ። ጋብቻ አይፈጽሙበትም።በሀገራችን ይኸን የመሰለ የጋብቻ መከልከል የሚያደርግ፤የሸዋ ጠቅላይ ግዛት በተለይም አዲስ አበባ ነው ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ የማያርሱት ፤ የማይቆፍሩት ፤ አንጥረኞች ሸማኔዎች ፤ በጠቅላላ የእጅ ሥራ ብቻ የሚያዘወትሩት በዚህ ወር ስለሚጋቡ የአንጥረኞች የጋብቻ ጊዜ ነው ብለው የሚያምኑ አሉ ።

ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ፤



www.ethiopianorthodox.org

# ቡ ሄ

በየዓመቱ ነሐሴ ፲፫ ቀን የሚከበረው መንፈሳዊ በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስያሜ «ደብረ ታቦር» በሕዝቡ ዘንድም ቡሄ ተብሎ ይጠራል ። ሁለቱም አጠራር የበዓሉን ሥርወ ታሪክ የጨበጠ ነው ። መብረቅ ሲፈልቅ ፤ መብራት ሲበራ ፤ ፀሐይ ሲወጣ ፤ ቦግ አለ ማለት በአማርኛችን የተለመደ ነው ። ስለዚህ ቡሄ በርሀ ከሚለው የግእዝ ወይም ቦግ አለ ከሚለው ያማርኛ ቃል የተወሰደ ሕዝባዊ አነጋገር ይመስላል ።

በዚህ ዕለት ችቦ ይበራል ፤ ዳቦ ይጋገራል ፤ ልጆች ቡሄ በሉ እያሉ ይጮኻሉ ። ሰሞኑን ሁሉ እረኞች ቡሄ ተብሎ የሚጠራውን ከወላጆች ከዘመድ አዝማድ ፤ ወይም ከጐረቤት የሚሰጣቸውን ዳቦ ይዘው ወደዱር ይሔዳሉ ። ኅብስቱንም እየበሉ ይጨፍራሉ ። ጅራፍም ያጮኻሉ ለዚህም የት መጣሹን ስንሻ ፤ በሊቃውንቱም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ የተለያየ አስተያየት እናገኛለን ።

ሕዝባዊ አስተያየት ፤ እረኞች ምን አሉ ? ጌታ በተወለደ ጊዜ መልአክ አትፍሩ ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁ ፤ ስለአላቸው ፤ ከዚህ የተያያዘ ይመስላል ። በሀገራችን እረኞች በልዩ ልዩ ጨዋታ መልክ የሚናገሩት ሁሉ ተደማጭነት አለው ። ስለዚህ በዘመናት መካከል አንድ አገልጋይ ቅን ሠራተኛ ከመሆኗ የተነሣ ፤ የተመደበላት ሥራ ሁሉ በተአምራት እየተከናወነ ስለተገኘ አሠሪዎቿ የድካሟ ዋጋ የሚሆን ዱቄት ከለከሏት ። እርሷም እረኞች ይፍረዱኝ ብላ ክሱን ወደ እረኞች አቀረበች ። ልጆቹም በምንስ ዓይነት የታዘዘችውን ከፈጸመች እንዴት የድካሟን ዋጋ ትከለከላለች ብለው ፈርደውላት ዱቄቷን ስለ አገኘች ፤ በፍርዳቸው ተደስታ ይህንስ ስለትክክለኛ ፍርዳችሁ ለእናንተው ዳቦ ጋግሬ ለማብላት እንጂ ፤ ራሴ አንድ ጠቀምበት አልፈልግም ስለአለቻቸው ፤ ከእረኞቹ መካከል አንዱ ተነሣና በዘመኑ ቋንቋ በግእዝ «አሆ በሉ» ማለት እሽ በሉ ስለአለ ተደስተው አሆ በሉ እያሉ ጨፍረው ነበር ። አሁንም በአንዳንድ አውራጃዎች አሆ በሉ እያሉ ነው የሚጮሁት ። ይህ ሲያያዝ መጥቶ ነው የሚሉ አሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ በሀገራችን ከግንቦት እስከ ነሐሴ ድረስ የዘር ጊዜ በመሆኑ ፤ በሬና የገበሬ ሥራ ከባድ ነው ። ከዚህ በኋላ ግን በመስከረም አዲስ መሬት ፤ ወይም እዳሪ የማውጣቱ ሥራ እስኪጀመር ድረስ የበሬ እረፍት የሚባል ጊዜ በዚሁ በደብረ ታቦር ሰሞን አለ ። በዚህ ወር ሣር ከማመቸቱም በላይ ፤ በሬ የገብስ ጠረሽ (ቂጣ) በጨው እየተጋገረለት ይበላል ይቀለባል ። ጥጋብም ስለሚሰማው በየመስኩ «ቡ» እያለ ያገሣል ። በዚህ ጊዜ እረኞች ደግሞ ለእኛስ ለጠባቂዎች ለምን ዳቦ አይጋገርልንም እያሉ ወላጆቻቸውን ስለሚያስቸግሩ ፤ የደብረ ታቦር ዕለት ብቻ ሳይሆን ሰሞኑን ሁሉ ዳቦ እየተጋገረላቸው ወደ ዱሩ እየወሰዱ ይበላሉ ። ባለጉም መጋረጃቸው ክረምት እያቃለለ ሔደ ፤ ብርሃን ሊወጣ ነው ደስ ይበላችሁ ። ስለዚህም እንደበሬ «ቡ» እያላችሁ አግሡ ይላሉ ። የደስታም መግለጫ ጅራፍ ያጮኻሉ ። ያባቶችም ምሳሌ «ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ፤ ቡሄ ከዋለ የለም ክረምት» ይላል። ይኸም የሚያመለክተው እንደእረኞቹ ያለ አስተያየት ነው የሚሉ አሉ ።

በቤተ ክርስቲያን ፤ በመሠረቱ በዓሉ በቤተ ክርስቲያናችን የሚከበረው፤ ወንጌላውያኑ እንደገለጹት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተወለኑ ነቢያትና ሐዋርያት ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር ሲገልጽ ፊቱ እንደ ፀሐይ አበራ ፤ ልብሱም እንደበረዶ ነጭ ሆነ በማለት አስተማሩ ። ይህን ለማስታወስ ሲሆን ፤ ችቦም የሚበራው ብርሃነ መለኮቱ በተገለጠ ጊዜ አብረውት የነበሩት ሁሉ ሊያውት ያልቻሉት ኃያል ብርሃን አንፀባርቆ እንደነበር የሚያዘክርነው።

«ቡሄ» በሚል ስያሜ ስለሚዘጋጀው ኅብስት (ዳቦ) ግን በሊቃውንቱም የተለያየ አስተያየት ይሰጣል ። አንዳንድ ሊቃውንት በአሪቱ ከፋሲካ በኋላ አምሳ ቀናት ቆይቶ በዓለ ሰዊት በሚል ስያሜ የሚከበር የሸት ፤ ወይም የአዲስ እህል መታሰቢያ ነበርና ያ ሲያያዝ መጥቶ እኛም ክረምቱ ተገባድዶ ባይበዛ በቆላ ሀገር በተሎ የሚደርሱ እንደበቆሎ ያሉትን የአዲስ እህል እሸት ፤ ለመብላት የምንችለው ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ በመሆኑ በዓሉንከበዓል በመደመር ኅብስት ወይም ዳቦ እያዘጋጀን የምናከብረው በአሪቱ ይደረግ የነበረውን በመከተል ነው ። በአሪቱ ይጋገር የነበረው ያልቦካ እህል ነው ። ይህም ያልቦካ እህል በቋንቋችን ቡሆ ስለሚባል ልጆች ቡሄ በሉ እያሉ የሚጨፍሩት ቡሆ ካለው ነው በማለት አስተያየት ይሰጣሉ ።

የብዙዎቹ ሊቃውንት አስተሳሰብ ግን በደብረ ታቦር ከተፈጸመው ድርጊት ጋር የተያያዘ ወደ መሆኑ ፤ ያዘነብላል ። ይኸውም ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበት ተራራ ደብረ ታቦር አግጣጫ መንጋ ይጠብቁ የነበሩ እረኞች ከብርሃኑ ብዛት የተነሣ ቀኑንና ሌሊቱን ለመለየት ተስኗቸው ወደየቤታቸው ስለአልመጡ ፤ ወላጆቻቸው ለእራታቸው የሚሆን ዳቦ እየያዙ ሔደው ነበርና ያንን ለማስታወስ ነው የሚል አስተያየት ይገኛል ።





www.ethiopianorthodox.org

«እሆ በሉ» በአንድ አንድ አውራጃ ደግሞ በዚሁ ዕለት ልጆች የሚጨፍሩት እሆ በሉ በማለት ነው ። ይህንም ሊቃውንቱ ሲተረጉሙ ብርሃነ መለኮቱ በደብረ ታቦር በተገለጠ ጊዜ «መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል ፤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ» የምወደው ልጅ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ቃል ተሰምቶ ነበርና ፤ እሆ በሉ ማለት እሽ በሉ ስለ ሆነ ፤ ከዐዋቂዎች ወስደው ይጠቀሙበታል ። ትምህርቱም እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ሁሉ ፈጽሙ ማለት ነው ይላሉ ።

ጅራፍ ፤ ማጮህ ከቡሄ ጀምሮ ሰሞኑን ሁሉ እረኞቹ ዳቦ ይዘው ወደዱር ይሔዳሉ ። ከዚያም ካንድ ላይ ሆነው ይመገባሉ ። ጅራፍም እያጮሁ ይጫወታሉ ። ይህንም ሊቃውንቱ ሲተረጉሙ በዚያው በደብረ ታቦር «ወከኑ ሙሴ ወኤልያስ እንዘ ይትናገሩ ምስሌሁ» ሙሴና ኤልያስ ወደፊት የሚደርስበትን የጌታችንን ፀዋትወ መከራ በማውሳት በእኛ ላይ አድረህ ብዙ ተአምራት እንዳልሠራህ ሁሉ ፤ በሰው እጅ ልትወድቅ ነው ? በማለት ይናገሩ ነበር ። ስለዚህ ልጆች የሚያጮሁት ጅራፍ የጌታችን ግርፋት ሲያመለክት ፤ ኀብስቱም ሥጋውን ቆርሶ ፤ ደሙን አፍስሶ ለሰው ድኅነት ራሱን አሳልፎ መስጠቱን ለማሰብ ነው ይላሉ ።

ሊቃውንቱና ሕዝቡ ስለ በዓሉ መነሻ የሚሰጡት ምክንያት ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሲሆን ፤ ይህ ሁኔታ ከመቼ ጀምሮ ነው የሚሠራበት ለሚለው ጥያቄ ግን የሊቃውንቱ አስተያየት ከአራት ተያይዞ መጣ ፤ ከክርስትና ጋር ገባ የሚል ልዩነት ስለአለበት ። በዚህ ጊዜ ነው ብሎ የተወሰነ አስተያየት ለመስጠት አልተቻለም ። ሁኔታው በመሠረቱስ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው ? ለሚለው አስተያየት ፤ ደግሞ ክርስቶስ ሕሙማንን በመፈወስ ፤ ሙታንን በማስነሣት ብቻ ሳይሆን ፤ ሰው አይቶ ሊመለከተው የማይቻል መለኩቱን በመግለጥ አምላክነቱን ያረጋገጠበት ዕለትና ቦታ ድርጊት የምናስታውስበት በመሆኑ ፤ ጥቅምን ሲይዝ ፤ በአንድ በኩል ደግሞ በዓሉ የሚውልበት ወር ውኃ ሙላት የሚበዛበት ሲሆን ፤ እናቶች ለዘመድ ፤ አዝማድ ልጆች ዳቦ ይዘው ካንዱ ወደ አንዱ ሲዘዋወሩ በውኃ ሙላት እየተጠለፉ የብዙዎቹ ቤት መፍረሱ ጉዳት ነው ።

ስለዚህ ራሳችንን ከጉዳት ላይ ከመጣል ተጠብቀን በዓሉን ለማክበር በተለይ የመገናኛ ችግር ባልተቃለለበት ቦታ ያለን መዘዋወሩን ትተን በዓሉን በቤታችን ማክበር አለብን ።

አእምሮ ማንደፍሮ ፤



www.ethiopianorthodox.org